# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 320 ሐምሌ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ- ከፋይል

## “አንገብጋቢ የኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ባለበት አገር ያለውን ውስን ሀብት በሃላፊነት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል”

-አቶ ክርስቲያን ታደለ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- አንገብጋቢ የኢኮኖሚ ጥያቄ ባለባት ሀገራችን ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል በየደረጃው ያለው አመራር በሃላፊነት መስራት እንደሚጠበቅበት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡ በወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ችግር ያለባቸው 39 ተቋማት በገንዘብ ሚኒስቴር ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረጉንም አስታውቋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ በርካታ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍላጎቶች ባሉበት ግን ደግሞ ያለውን ውስን ሀብት በሃላፊነት ጥቅም ላይ ያለማዋል ችግር መኖሩን ቋሚ ኮሚቴው በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ክትትል ለመገንዘብ ችሏል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች በብዙ ተቋማት ፍላጎትን መሰረት

«አንገብጋቢ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በሻምፒዮናው ኢትዮጵያን ሳኮራው ልዑክ ልዩ አቀባበል እንደሚደረግ ተገለጸ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ልዑክ ላሳዩት ሀገራዊ አንድነትና ላስገኙት ውጤት ተገቢና ልዩ አቀባበል እንደሚደረግላቸው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፣ 18ኛው የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ለተሳተፈው የኢትዮጵያ ልዑክ ልዩ አቀባበል ይደረጋል።

ሚኒስትሩ በሻምፒዮናው ለተገኘው ውጤት መላው ኢትዮጵያውያንን እንኳን ደስ አላችሁ ብለው፣ በተለይም ኢትዮጵያውያን በሻምፒዮናው መድረክ ባስመዘገቡት ውጤትና ሀገርን በማስቀደም ያሳዩት አንድነት የዓለም አይን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለከት ከማድረጉም በላይ ለአንድ ዓላማና ሀገራዊ ፍቅር መቆማቸው እንዲሁም ያሳዩት ስፖርታዊ ሥነ-ምግባር ሀገርን የሚያኮራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም የልዑክ ቡድኑ ወደ ሀገር ሲመለስ ልዩ የሆነ የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን እና የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ አትሌቶችና ለልዑካን ቡድኑ አባላት የሽልማት መርሀ ግብር የተዘጋጀ መሆኑን ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ለአትሌቶቹ ከሌላው ጊዜ በተለየ የላቀ አቀባበል




ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ለዚህም አትሌቶቹና ሌሎች የልዑካን ቡድኑ አባላት ከፍተኛ ውጤት ከማምጣታቸው በተጨማሪ በቡድን ስራና ለሰንደቅ ዓላማ ክብርና ፍቅር ያሳዩት ተግባር የሚደነቅ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በሻምፒዮናው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# የሩሲያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አዲስ አበባ ገቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የሩሲያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ትላንት ምሽት አዲስ አበባ ገቡ።

የሩሲያው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ዳያስፖራው በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ ቀረበ

ገጽ 4

ዜና

# በኦሮሚያና ሶማሌ በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሚሰጠው ትኩረት እንዲጠናከር ኢሰመኮ አሳሰበ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሚሰጠው ትኩረትና ምላሽ አሁንም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን አሳሰበ።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በድርቁ በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ደርሶባቸዋል ተብለው በተለዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ያዘጋጀውን ለተቋሙ በዓይነቱ የመጀመሪያው የሆነውን የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ዘርፍ ሪፖርት ይፋ አድርጓል።

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው፤ እስካሁን በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት በድርቁ ለተጎዱ ሰዎችና አካባቢዎች የተሰጡ ምላሾች አበረታች መሆናቸውን ጠቁመው፤ ለምላሹ ግን ይበልጥ ጥረት መደረግ እንዳለበት ማሳሰባቸው ተገልጿል።

ተጎጂዎች አሁንም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙና ድርቁም ከሁለቱ ክልሎች በተጨማሪ ወደሌሎች አካባቢዎች እየተስፋፋ መሆኑን ኮሚሽነሩ አስታውቀው፤ በተለያዩ ጊዜያት በሚያገረሹ ግጭቶች ምክንያት በድርቁ ሳቢያ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለተደራራቢ ጉዳት እየዳረገ ነው፤ ስለሆነም በድርቁ ለተጎዱና አዋሳኝ አካባቢዎች የሚሰጠው ትኩረት ሊቀንስ አይገባም ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ከሆነ፤ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በሕጉ መሰረት የድርቁን አደጋ በይፋ በማሳወቅ



እገዛ ከሚያደርጉ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲያደርጉ የማድረግ ግዴታ አለበት።

በድርቁ ሳቢያ ለተፈናቀሉ ድጋፍ ፈላጊዎች ባሉበት ቦታ ቀጣይነት ባለው መልኩ እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል ሲል ኢሰመኮ በሪፖርቱ አመላክቷል።

በሪፖርቱ መሰረት፤ በድርቁ ጉዳት ሳቢያ በተለይ በቂ ውሃና ምግብ ባለመኖሩ ሰዎች ለተለያዩ የጤና እክሎች ተዳርገዋል፡፡ በምግብ እጥረት የተጎዱ ሰዎች አሉ፡፡ የጤና ግልጋሎት መስጫ ተቋማት በአካልም በኢኮኖሚም ተደራሽ አለመሆናቸውንም ክትትሉ አሳይቷል፡፡

በዚህ ምክንያት ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም አረጋውያንና ሕፃናት ሕይወታቸው አደጋ ላይ ወድቋል። በድርቅ ምክንያት ተፈናቅለው በካምፖች የተቀመጡ በቂ የጤና አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል ሲል ኢሰመኮ አሳስቧል።

የፌዴራልና የየክልል መንግሥታቱ በአፋጣኝ ሊተገብሯቸው ይገባል ካሏቸው ተግባራት መካከል አንዱ በመረጃና በምዝገባ ሥርዓት የታገዘ፣ አሳታፊ የሆነ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት የተዘረጋለት እንዲሁም ከፍላጎት ጋር የተመጣጠነ ምላሽ ማቅረብ ያስፈልጋል ሲል ኢሰመኮ አስታውቋል።

በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን፣ በያቤሎ፣ ተልተሌ፣ ድቡሉቅ፣ ድሬና ሞያሌ ወረዳዎች በሚገኙ 11 ቀበሌዎች፤ እንዲሁም በሶማሌ ክልል፣ ሸበሌ፣ ጀረር እና ፋፈን ዞኖች፣ በጎዴ እና አዳድሌ፣ ደጋሃቡር እና ቢርቆድ እና ቀብሪ በያህ ወረዳዎች በሚገኙ ስድስት ቀበሌዎች ምርመራ መደረጉን ኢሰመኮ ገልጿል።

በዚህም መሰረት ተጎጂዎችን፣ የመንግሥት አካላትን፣ የጤና ተቋማት ኃላፊዎችን እንዲሁም የተለያዩ ድጋፎችን የሚያቀርቡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የኢሰመኮ ሰዎች ማነጋገራቸውና ምልከታ ማድረጋቸው ተመላክቷል።

እንደ ኢሰመኮ ከሆነ፤ በድርቁ ቅድመ ማስጠንቀቅና በዝግጁነት ረገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 363/2008 ድንጋጌዎች መሰረት የድርቁን አደጋ ቅነሳ፣ ቅድመ-ማስጠንቀቂያና ዝግጅት እንዲሁም የማሳወቅ ሥራዎች በይፋ አለመሠራታቸው ታይቷል፡፡

ክትትል የተደረገባቸው ቦታዎች በተደጋጋሚ ጊዜያት በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች መሆናቸውን ያመለከተው ሪፖርቱ፤ ድርቁ ከዚህ በፊት ከነበሩት አደጋዎች በተለየ መልኩ ከሁለት እስከ አራት የዝናብ ወቅቶች ያልዘነበበት እንዲሁም ሰፊ ቦታዎችን ያካለለ እንደሆነ የክትትሉ ግኝት እንደሚያሳይ ኢሰመኮ አስታውቋል።

በመሆኑም ማሕበረሰቡ እንደ ከዚህ ቀደሙ ወደ ተሻሉ ቦታዎች ተዘዋውሮ ከድርቁ ተጽዕኖ ለማምለጥ እንዳልቻለ በመጠቆም፤ ያልተቋረጠ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ኢሰመኮ ገልጿል።

ኢሰመኮ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ ከየካቲት 14 እስከ 29 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ በድርቁ በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ደርሶባቸዋል ተብለው የተለዩ አካባቢዎች ላይ ያደረገውን ክትትል በተመለከተ ባለ 50 ገጽ ሪፖርት ትናንትና ይፋ አድርጓል።

# “ኢትዮጵያ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን ግጭት በሰላም አማራጭ ለመፍታት መወሰኗ የቀጣናው ሰላም ተምሳሌትነቷን ዳግም የሚያረጋግጥ ነው”

**- አለልኝ አድማሱ**
**በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር**

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን ግጭት በሰላም አማራጭ ለመፍታት መወሰኗ የቀጣናውና የዓለም ሰላም ተምሳሌትነቷን ዳግም የሚያረጋግጥ መሆኑን በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ ገለጹ።

እስራኤል በኢትዮጵያ ግጭቶችን በሰላም አማራጭ ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችን እንደምትደግፍም አምባሳደሩ አረጋግጠዋል፡፡

መንግሥት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ሀገር ሽማግሌዎች በመላክ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን ያስታወሱት አምባሳደር አለልኝ፤ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላም ቢሆን የተናጠል ተኩስ አቁም በማድረግ ቁርጠኝነቱን በተግባር ማሳየቱን ጠቁመዋል፡፡

አሁን ላይ ደግሞ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮችን፣ አለመግባባትና ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታትና ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ መሆኑ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ከኢዜአ ጋር ቆይታ ያደረጉት በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ፤ ሀገራቸው እስራኤል የሰላምንና የትብብርን አስፈላጊነት በአግባቡ ትገነዘባለች፤ ከዚህ አኳያ በዙሪያዋ ካሉ የዓረቡ ዓለም አገራት ጋር በቅርበት እየሰራች ነው ብለዋል።

ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ለመካከለኛው ምስራቅ ቀጣና ቅርብ የሆነችው ኢትዮጵያ ችግሮችን በሰላም አማራጭ ለመፍታት እያደረገች ያለውን ጥረት አድንቀዋል፡፡

መንግሥት የጀመረው የሰላም አማራጭ ሂደት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚጠቅም መሆኑን አንስተው፤ የሰላም አማራጩ ለጎረቤት ሀገራት፣ ለአፍሪካና ለቀጣናው አስተማሪ ነው ብለዋል።

እስራኤል የኢትዮጵያን የሰላም አማራጭ መንገድ



እንደምትደግፍ ያነሱት አምባሳደሩ፤ የኢትዮጵያ ሰላም መሆን መንግሥት ፊቱን ወደ ልማት ሙሉ ለሙሉ ለማዞር ያስችለዋል ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ በሀገሪቱ ሰላም ሲሰፍን ሌሎች ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን የልማትና ሌሎችም ትብብሮች እንደሚያጠናክር ነው ያብራሩት።

“ኢትዮጵያ አፍሪካን አንድ ያደረገችና በሰላም አብረን እንኑር የምትል የሰላም ምልክት ናት” ያሉት አምባሳደር አለልኝ፤ በዓለም ሰላም ማስከበር ያላትን ሚናም አድንቀዋል።

ኢትዮጵያ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን ግጭት በሰላም አማራጭ ለመፍታት መወሰኗ የቀጣናውና የዓለም ሰላም ተምሳሌትነቷን ዳግም የሚያረጋግጥ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

መንግሥት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽንን በማቋቋም ወደ ሥራ የገባ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ችግር በአፍሪካ ሕብረት አስተባባሪነት በሰላም አማራጭ ለመፍታት ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወቃል፡፡

# “በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተው የመረጃ ጦርነት በሳይበር ደሕንነትና ሌሎች ተቋማት የጋራ ጥረት እየተመከተ ነው”

**- ሰላማዊት ካሳ**
**የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ**

በጋዜጣው ሪፖርተር




አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተው የመረጃ ጦርነት በሳይበር ደሕንነትና ሌሎችም ተቋማት የጋራ ጥረት እየተመከተ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሣ፣ መንግሥት ጦርነቱን ለመመከትና ሕግ ለማስከበር ብርቱ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው ያስረዱት።

ቴክኖሎጂን በመጠቀምና ትክክለኛ ፈጣን መረጃን ወደ ሕዝብ በማድረስ የመረጃ ጦርነቱን ለመመከት ስልት ተነድፎ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ጠላቶች በሀሰተኛ መረጃ ሕዝቡን ለመከፋፈል የተለያዩ ጥረቶችን እያደረጉ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ የመረጃ ጦርነቱ አገር ለማፍረስ ከፍተኛ ገንዘብ ተመድቦለት በተቀናጀ መንገድ እየተካሄደ መሆኑን አብራርተዋል።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተው የመረጃ ጦርነት በሳይበር ደሕንነት ተቋማትና በሌሎችም የጋራ ጥረት እየተመከተ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

መንግሥት የጠላትን የመረጃ ጦርነት ለመመከት ተቋማትን በማጠናከር ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትና የኢንፎርሜሽን መረብ ደሕንነትን የመሳሰሉ የመረጃ ደሕንነት ተቋማት በተቀናጀ መልኩ በልዩ ትኩረት እየሠሩ ስለመሆኑም ተናግረዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የመረጃ ትክክለኛነትን ማጣራት፣ ለሕዝብ ፈጣን መረጃዎችን ማድረስና አጀንዳ መቅረጽ ላይ የበኩሉን ሚና እየተወጣ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የመረጃ ጦርነቱን በመመከት ሂደት የመገናኛ ብዙሃንም የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰጡት ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ የተከፈተባትን የተቀናጀ ግራጫ ጦርነት እየተፋለመች መሆኗን መግለፃቸው ይታወሳል።

ዜና





ዶክተር ሶፊያ ካሳ

# 50 ሺህ ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ ከሶስት ቀን በኋላ ጅቡቲ ይደርሳል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ግዥ ከፈጸመበት 12 ነጥብ 87 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ የመጨረሻውን ዙር 50 ሺህ ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ የያዘች መርከብ ከሶስት ቀን በኋላ ጅቡቲ ወደብ እንደምትደርስ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የበቆሎ ምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት በማጋጠሙ አርሶአደሩ ሰብል ቀይሮ እንዲዘራ ጥረት መደረጉ ተገልጿል።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ መንግሥት ግዥ ከፈጸመበት የማዳበሪያ ግብዓት ውስጥ የመጨረሻ ዙር የሆነው ጭነት እ.አ.አ ነሐሴ 30 ቀን 2022 ጅቡቲ ወደብ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል።

መንግሥት ለ2014/15 የምርት ዘመን ግዥ ከፈጸመበት 12 ነጥብ 87 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ አብዛኛው ወደአገር ውስጥ ገብቶ የስርጭት ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ቀሪው ግብዓት በፍጥነት ገብቶ ለአርሶአደሩ እንዲሰራጭ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አይነት የማዳበሪያ አጠቃቀም ሂደት መኖሩን የገለጹት ዶክተር ሶፊያ፤ አርሶአደሩ በዘር ወቅት እና በቡቃያ ወቅት ማዳበሪያዎችን እንደሚጠቀም አስረድተዋል።

በዘር ወቅት ጥቅም ላይ ለሚውል ግብዓት ሰባት ነጥብ 87 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በአገር ውስጥ ገብቶ ለክልሎች መሰራጨቱንም ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል።

በአንፃሩ በቡቃያ ወቅት ጥቅም ላይ ለሚውል ግብዓት አምስት ሚሊዮን ኩንታል ዩሪያ ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል። ከዚህ ውስጥ 450 ሺህ ሜትሪክ ቶኑ አሊያም አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታሉ አገር ውስጥ ገብቷል። ቀሪው 50 ሺህ ሜትሪክ ቶኑ ደግሞ ወደብ ላይ ከደረሰ በኋላ ወደተለያዩ መጋዘኖች እንዲገባና አርሶአደሩ ጋር እንዲደርስ ክትትል ይደረጋል ብለዋል።

የፌዴራል ግብርና ሚኒስትር ማዳበሪያ የማሰራጨቱን ኃላፊነት ስለማያከናውን ለአርሶአደሮቹ እያደረሱ የሚገኙት ክልሎች ናቸው ያሉት ዶክተር ሶፊያ፤ ይሁንና ሚኒስቴሩ ስርጭቱን በተመለከተ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል። እንደአየአካባቢዎቹ ሁኔታ ቀድሞ የሚዘሩ አካባቢዎች ላይ ማዳበሪያው እንዲደርስ ጥረት ተደርጓል ሲሉም አስረድተዋል።

የማዳበሪያ ስርጭቱ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ነው አይባልም፤ አንዳንድ መንገራገጮች ይኖራሉ ያሉት ዶክተር ሶፊያ፤ ችግሮችን ለማስቀረት ሚኒስቴሩ ግብረኃይል በማቋቋም በየጊዜው ክትትል እያደረገ ግብረ መልስ እየሰጠ መሆኑን አስታውቀዋል። በግብረኃይሉ መሰረት እንደየክልሎቹ ሁኔታ የተለያዩ ክፍተቶች ቢኖሩም የማዳበሪያ ስርጭት ችግሮች እንዲሻሻሉ መመሪያ እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዶክተር ሶፍያ እንደገለጹት፤ የማዳበሪያ አቅርቦት የክልሉን ፍላጎት መሰረት አድርገን እናቀርባለን፤ ስርጭት ላይ ግን ክፍተት ሊፈጠር ይችላል። የማዳበሪያ አቅርቦት እጥረት ሲፈጠር በክልሉ መጋዘን ውስጥ ያለው ማዳበሪያ ቀድመው ወደሚዘሩ አካባቢዎች በማጓጓዝ ችግሩን መፍታት እንደሚያስፈልግ መመሪያ ተላልፏል ብለዋል።

ማዳበሪያው መገዛቱ ብቻ ትርጉም አይኖረውም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በዋናነት አርሶአደሩ ጋር ደርሶ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ለዚህም ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ማዳበሪያ ስርጭቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሳካ ጥረት ማድረግ አለባቸው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተመሳሳይ ምርጥ ዘር ለአርሶአደሩ የማከፋፈል ሥራው በዋናነት የክልሎች ኃላፊነት ነው። አብዛኛው የምርጥ ዘር አቅርቦት በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ቢሆንም በዚህ ዓመት የበቆሎ ምርጥ ዘር እጥረት አጋጥሟል። ችግሩ በአንዳንድ አካባቢዎች በተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች የተነሳ ምርት በአግባቡ ባለመሰብሰቡ የተፈጠረ ነው ብለዋል፡፡

ሆኖም ችግሩን ለማስተካከል አማራጮች ተወስደዋል። በአንድ በኩል አገራችን ባሉ የምርምር ማዕከላት የተለቀቁ ዝርያዎችን ከተለያዩ አካባቢዎች እንዲጠቀምና ያንን ማግኘት ባልተቻለበት ሁኔታ ላይ በተወሰኑ አካባቢዎች አርሶአደሩ ሰብል ቀይሮ እንዲዘራ ተደርጓል ብለዋል።

በ2014/15 የምርት ዘመን ግዥ ከፈጸመበት የማዳበሪያ ግብዓት ውስጥ የመጀመሪያውን 50 ሺህ ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ የየያዘችው መርከብ ጅቡቲ ወደብ የደረሰችው ሚያዚያ ወር አጋማሽ ላይ ነበር።

# "የዋጋ ግሽበቱ መንስኤ መዋቅራዊ በመሆኑ የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል"

**- ዶክተር ደግዬ ጎሹ**
**የምርምርና የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ተንታኝ**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የዋጋ ግሽበት መንስኤ መዋቅራዊ በመሆኑ የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለመገንባት በትኩረት ሊሰራ ይገባል ሲሉ የምርምርና የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ተንታኝ የሆኑት ዶክተር ደግዬ ጎሹ ተናገሩ።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር የምርምርና የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ ተንታኝ የሆኑት ዶክተር ደግዬ ጎሹ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የዋጋ ግሽበት ለረጅም ጊዜ ሲከማች የመጣ ፈርጀ ብዙ የሆነና መዋቅራዊ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት አንድ በአንድ የሚደረገው የፖሊሲ እርምጃ ብዙም ውጤታማ አይሆንም። ስለሆነም መዋቅራዊ የሆነውን የኢኮኖሚ ችግር መፍታት ሲቻል በኢኮኖሚው ላይ መሰረታዊ ለውጥ ይመጣል። ይህ ደግሞ ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ፖሊሲ ተነድፎ ሊሰራ ይገባል።

እንደ ምጣኔ ሀብት ተንታኙ ገለጻ፤ የሚወጡ የፖሊሲ እርምጃዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በኢኮኖሚው ላይ የሚስተዋሉ ህገ ወጥና ሰው ሰራሽ ችግሮችን መቆጣጠር መቻል ያስፈልጋል። በተለይ ሰው ሰራሽ ችግሮች በጣም ስለሚባባሱ መንግሥት በጉዳዩ ላይ የማያዳግም ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል። ለአብነት የዋጋ ግሽበቱን ለመግታት ፍራንኮ ቫሉታ ሲፈቀድ በየትኛው ዘርፍ ምን አይነት ሰው ማስመጣት እንዳለበት፣ በሸቀጦች ላይ ዋጋ የሚተመን ከሆነ መንግሥት እንዴት ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት




እንዲሁም በዋጋ ግሽበቱ የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዴት ሊደጎሙ እንደሚችሉ በፖሊሲ የተደገፈ አሰራር ሊበጅ ይገባል።

በጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ጣልቃ ገብነት እርምጃ መንግስት ሲወስድ ለማን እንዴት እንደሚወሰድና የተወሰደው ጣልቃ ገብነት ውጤታማ ሆኗል አልሆነም፣ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ምን መስራት አለበት፤ የሚሉ ጉዳዮችን አቀናጅቶ የሚሰራ መዋቅራዊ አሰራር መኖር መቻል እንዳለበትም አሳስበዋል።

ይህ ሳይሆን በተበታተነ መልኩ የሚሰራ ከሆነ ግን ውጤቱን መገምገም አይቻልም ያሉት ተንታኙ፤ የዋጋ ግሽበቱን የሚቆጣጠር በፖሊሲ የተደገፈ አካል ሊኖር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ደግዬ ማብራሪያ፤ ላለፉት ሶስት አስርት አመታት የተከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሚገባ በመገምገም ያንን ላለመድገም የሚሻሻለውን በማሻሻል የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለመገንባት በትኩረት መስራት አስፈላጊ ነው። በዚህ አመት የታየው የበጀት ጉድለት ሊያካክስ የሚችል የፖሊሲ እርምጃ መውሰድ ይገባል። ፡ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ሊደረግ ቢፈልግ እንዴት፣ ይተገበራል የሚለው በምን አይነት የፖሊሲ እርምጃ እንደተወሰደ ግልጽ አይደለም። ይህ የዋጋ ግሽበቱን ሊያዛባ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከፍተኛ ዋጋ ግሽበት ከሚታይባቸው ሀገራት አንዷ መሆኗን የጠቆሙት ዶክተር ደግዬ፤ የዋጋ ግሽበት የታየባቸው አገሮች በአብዛኛው አለመረጋጋት ያለባቸው ናቸው ብለዋል። ስለዚህ የዋጋ ግሽበቱን ፈጥኖ መቆጣጠር ካልተቻለ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ የሚወስድ ነው። በተለይም በአቅርቦት በኩል ያለውን ችግር መፍትታት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ሆኖ ሊሰራበት ይገባል ። የውስጥ ግጭቶችም ለዋጋ ግሽበቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ስላላቸው ችግሮቹ የሚወገዱበትን መፍትሄ መፈለግ ሌላኛው የመፍትሄው አካል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ደግዬ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት አንደኛውና ዋነኛው መነሻ የአቅርቦት ችግር ነው። ይህም ከማምረት ጋር የሚያያዝ፣ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ በምንዛሬ የሚገቡ ሸቀጦች ዋጋ መጨመር፣ የመሬት አቅርቦትና በአግባቡ ለምርት አለመጠቀም፣ የገንዘብ አቅርቦትና ቁጥጥርና መሰል ጉዳዮች ትልቅ ችግሮች ናቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የዋጋ ግሽበት ለረጅም ጊዜ ሲከማች የመጣ ፈርጀ ብዙ የሆነና መዋቅራዊ በመሆኑ የፖሊሲ እርምጃ በመውሰድ የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለመገንባት በትኩረት መስራት እንደሚገባ ዶክተር ደግዬ ጎሹ ገልጸዋል።

# የውሃና ኢነርጂ ሀብትን መረጃ ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ የሚያሳውቅ የሚዲያ ፎረም ሊቋቋም ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን የውሃና ኢነርጂ ሀብት ትክክለኛ መረጃን ሁሉንም ቋንቋዎች ተጠቅሞ ለማሳወቅ የሚያስችል የሚዲያ ፎረም እንደሚቋቋም የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ዶክተሩ ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለ ውሃና ኢነርጅ ሀብት የሚያስተዋውቅ የሚዲያ ፎረም ለማቋቋም ባዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ እንደገለጹት፤በኢትዮጵያ ያለውን የውሃና ኢነርጂ ሀብት ትክክለኛ መረጃ ለአጎራባች የአፍሪካና ለአረቡ አገራት በተገቢው መንገድ ለማሳወቅ የሚያስችል የሚዲያ ፎረም ማቋቋም አስፈላጊ ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካት በሚዲያ ተቋማት የሚሰሩ ጋዜጠኞች አገራችን ያላትን የውሃና ኢነርጂ ሀብት ቀድመው ሙሉ መረጃው ሊኖራቸው ይገባል።

ጋዜጠኞቹ ይህንን እውቀት ተጠቅመው ትክክለኛውን መረጃ ለህዝቡ፣ ለአጎራባች አገራት፣ ለአረቡና ለዓለም አገራት በተገቢው መንገድ ማሳወቅ እንደሚኖርባቸው ጠቁመው፤በተለይ የኢትዮጵያን መልማት የሚጠሉና እድገቷን የማይሹ አገሮች ለአረቡ ዓለምና ለዓለም አገራት ያስጨበጡትን የተዛባ መረጃ ማረምና እውነታውን የማሳወቅ ስራ ከጋዜጠኞችና ከሚዲያ ፎረሙ አባላት ይጠበቃል ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

የሚዲያ ፎረም በማቋቋምና አብሮ በመስራት ለጠላቶቻችን ቀድመን አጀንዳ ልንፈጥርላቸው ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ለሚከፍቱብን የሀሰት መረጃ ዘመቻም ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

ሚዲያዎች ማበርከት ያለባቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ፎረሙ አስፈላጊ ነው። በቅርቡ ተቋቁሞ ስራውን ይጀመራል ያሉት ሚኒስትሩ፣ የሁሉም ሚዲያ ጋዜጠኞችና የፎረሙ አባላት የውሃና ኢነርጂ አምባሳደሮች በመሆን በያሉበት ሁሉ የማገልገል አገራዊ ድርብ ኃላፊነት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር ኢንጀነር ሱልጧን ዋሊ በበኩላቸው ፣ ጠላቶቻችን እኛን ለማሳነስና እንዳናድግ ለማድረግ አይተኙም። እኛም ባሉን አራጮች ሁሉ በመጠቀም እውነቱን ለሁሉምና ለዓለም ለማሳወቅና ለማስገንዘብ መተኛት የለብንም ብለዋል።

የሚያደርሱብንን ዓለም አቀፍ ጫና ለመቋቋም ቀድመን በመስራትና ያደረሱብንን መቀልበስ መቻል አለብን ያሉት ዴኤታው፣ በአገራችን ጉዳይ ሚዲያዎችና በኃላፊነት የሚሰሩ ማሕበረሰብ አንቂዎች በጋራ በመሆን የሚከፈትብንን የሀሰት ዘመቻ ማምከን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ጠላቶቻችን ባሏቸው የሚዲያ አማራጮች ሁሉ ተጠቅመው በብሔርና ክልል ሊከፋፈሉን ይሞክራሉ፣ ተሰባስበን በመስራት እውነታውን ሳይወዱ ልናሳውቃቸው ይገባል፣ ለዚህም ትክክለኛው መንገድ በመሰባሰብና የሚዲያ ፎረም ማቋቋም ነው። ተጀምሯል፣ ተጠናክሮም ይቀጥላል ብለዋል።

ፎረሙ ከተቋቋመ በኋላ በምንና እንዴት ይሰራል የሚለውን አሰራርና አካሄድ በማበጀት ወደ ትግበራ እንገባለን ሲሉም ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል።

ያለንን የውሃና ኢነርጂ ሀብት ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በሁሉም ቋንቋዎች የኢትዮጵያን የፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህን ማሳወቅ ይገባናል ሲሉ ተናግረዋል።

# ዳያስፖራው በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ ቀረበ

ውብሸት ሰንደቁ





ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

አምባሳደር ብርቱካን አያኖ

አዲስ አበባ፡- የዳያስፖራው ማሕበረሰብ የሚኖር ባቸው ሀገራት የውስጥ ችግራቸውን የፈቱበትን መንገድ ልምድና ተሞክሮ በማጋራት በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጥሪ ቀረበ፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት እና የኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ በጋራ ያስተባበሩት "በሀገራዊ ምክክር የዲያስፖራው ሚና እና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ" በሚል ርዕስ ከዳያስፖራው ማሕበረሰብ ጋር በትናንትናው ዕለት ምክክር ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የከኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ ሰብሳቢና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ፤ የዳያስፖራው ማሕበረሰብ የተሸረሸሩ ሀገራዊ የምክክርና የውይይት ባህሎችን ለማዳበር የራሱን አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የዳያስፖራው ማሕበረሰብ የሚኖርባቸው ሀገራት የውስጥ ችግራቸውን የፈቱበትን መንገድ ልምድና ተሞክሮ በማጋራት በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ለዳያስፖራው ማሕበረሰብ በተደረጉ ታላላቅ ጥሪዎች በዳያስፖራውና በሀገር ቤት መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር ተችሏል ያሉት አምባሳደር ብርቱካን፤ ኢትዮጵያ በመደበኛ መንገድ ከሚካሄደው የዳያስፖራው ተሳትፎ በተጨማሪ በተደረጉ ታላላቅ ጥሪዎች ዘርፈ ብዙ ትርፍ አትርፋለች ብለዋል።

ተመሳሳይ ጥሪዎች መከናወናቸው እውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ከመርዳታቸውም ባሻገር የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ላይ እና የሀገርን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ትልቅ ፋይዳ እንዳስገኘም አብራርተዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ብርቱካን ገለፃ፤ የከኢድ እስከ ኢድ ጥሪ እና ቀደም ብሎ የተደረጉ ታላላቅ ጥሪዎች ዳያስፖራው ለሀገሩ ባዳ እንዳይሆን እና ከከፍተኛ የሀገሪቱ ኃላፊዎች ጋር እንዲገናኝ እድል በመፍጠር በወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታዎች እና በመንግሥት ውሳኔዎች ላይ ግልጽነት እንዲፈጥር አድርጓል፡፡ ዳያስፖራው ይህን እድል በመጠቀም በሀገራዊ ምክክሩ ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

ዳያስፖራው እንደ አንድ ማሕበረሰብ የመደመጥና መረጃ የማግኘት መብቱ ተረጋግጦ አጋርነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናሉ ያሉት አምባሳደሯ፤ በቀጣይም ከዳያስፖራው ጋር የሚኖርባቸው ሀገራት ውስጣዊ ችግሮቻቸውን እንዴት እንደፈቱና ይህንን ከሀገራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ልንጠቀም የምንችልበት አግባብ ላይ ምክክሮች ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

የከኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ ሴክሬታርያት እና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሀመድ እድሪስ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት የተቋቋመበት ዋነኛው ተልዕኮ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና በሀገራቸው መካከል የድልድይነትና የአገናኝነት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ነው ብለው፤ ዳያስፖራው በሀገሩ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ላይ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ሀገራዊ አንድነትን አጠናክሮ ማህበራዊ ትስስርን ለማሳደግ እንዲሁም በሀገራዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለመምከር በዘንድሮው ዓመት ብቻ በበይነ መረብና በቀጥታ ውይይቶች ከ800 በላይ መድረኮች ተካሂደዋል ያሉት ዶክተር መሀመድ፤ ከ560 ሺህ በላይ የዳያስፖራ ማሕበረሰብ አባላትን በቀጥታ ማግኘት በመቻሉ ዳያስፖራው የተሻለ መግባባት ላይ እንዲደርስ አስተዋፅኦው የጎላ እንደነበር አንስተዋል፡፡

እንደ ዶክተር መሀመድ ገለፃ፤ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ሀገራዊ መግባባት የኢትዮጵያውያን አንድ አጀንዳ ነው በሚል ተቋቁሟል፡፡ የመድረኩ ዋነኛ ዓላማም ዳያስፖራውን ማሕበረሰብ ከኮሚሽኑ ጋር ማስተዋወቅ ነው፡፡ በቀጣይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በራሱ መርህ፣ ነፃና ገለልተኛ መንገድ መሰረት የዳያስፖራውን ማሕበረሰብ በማወያየት ሃሳብ የሚወስድበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ዶክተር መሀመድ እድሪስ፤ ዳያስፖራዎች አሁን የሚኖሩባቸው ሀገራት በአንድ ቀን የተገነቡ እንዳልሆኑ ጠቅሰዋል። ዛሬ በሰላምና በልማት የምናውቃቸው ሀገራት ቀደም ሲል የቁርሾና የጥላቻ መናኸሪያዎች እንደነበሩ ጠቁመው ሆኖም ሀገራቱ አሁን ላሉበት ደረጃ ያበቃቸው ምክክር ነው ብለዋል።

ዳያስፖራው ማሕበረሰብ ከሚኖርባቸው ሀገራት ያገኛቸውን ልምዶች እንደሚያካፍል እና ትልቅ ግብዓት ይኖረዋል ተብሎ እንደሚታመን ገልፀው፤ የዳያስፖራው ማሕበረሰብ በቀጣይ በሚኖሩ የሀገራዊ ምክክር መድረኮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## የሩሲያው ውጭ ጉዳይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሰርጌይ ላቭሮቭ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች አቀባበል አድርገውላቸዋል።

የሩሲያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሚኖራቸው ቆይታ በሩሲያ እና ኢትዮጵያ መካከል ስላለው የሁለትዮሽ ግንኙነት እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ከኢትዮጵያ መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡



## በሻምፒዮናው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአቀባበል መርሃ ግብሩን ይፋ ያደረጉት በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አማካሪ አቶ ሰለሞን አልዩ፣ ከውጤት አንፃርም በታሪክ ከፍተኛው ሜዳሊያ የተመዘገበበት በመሆኑ በተለየ መልኩ አቀባበል ለማድረግ መታሰቡን ገልጸው፣ ብሔራዊ ቡድኑ ዛሬ ሐምሌ 20/2014 ዓ.ም ከምሽቱ 3:00 ሰዓት ላይ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በሚደርስበት ወቅትና በማግስቱ ሐሙስ ልዩ አቀባበል እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

በመጀመሪያው እለት ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የዘርፉ አመራሮች በተገኙበት በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፍያ በመገኘት የክብር አቀባበል የሚደረግላቸው ሲሆን በማግስቱ ደግሞ በአዲስ አበባ በተመረጡ ዋና ዋና ጎዳናዎች በመዘዋወር ሕዝቡ አቀባበል እንዲያደርግላቸው የተመቻቸ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተለይም ከተዘጋጀላቸው ልዩ ማረፍያ እስካይ ላይት ሆቴል-በቦሌ ጎዳና ወደ አስጢፋኖስ በመጓዝ በአራት ኪሎ ወደ ፒያሳ እንዲሁም በቸርችል ጎዳና ወደ ለገሀርና መስቀል አደባባይ በመሄድ መጨረሻ ላይ በቤተ-መንግሥት ልዩ የምስጋናና የሽልማት መርሃ ግብር እንደሚከናወን አስታውቀዋል፡፡

አለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ሲካፈል የቆየው የኢትዮጵያ ቡድን 4 ወርቅ፣ 4 ብር፣ 2 ነሃስ፣ በድምሩ 10 ሜዳልያዎችን በመውሰድ ከዓለም አዘጋጇ አሜሪካን በመከተል 2ኛ ደረጃ ይዞ ማጠናቀቁ ይታወሳል፡፡

## "እንገብጋቢ የኢኮኖሚያዊ ጥያቄ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያላደረጉ ግዥዎች እንደሚፈጸሙ ሁሉ በአንዳንድ ተቋማት ደግሞ ጥራታቸው የወረደ እቃዎች የመግዛት ችግር አለ ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የተገዛውን እቃ በአግባቡ ካለመጠቀማቸው የተነሳ የሳርና የአፈር ሲሳይ ሲሆኑ ለማየት ተችሏል ብለዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ቁልፍ ተግባር መወቀስ ሳይሆን ማገዝ፣ ማስጠየቅ ሳይሆን ምክረ ሃሳብ ማስታጠቅ መሆኑን የተናገሩት አቶ ክርስቲያን፣ ከዚህ አንጻር የዋና ኦዲተርን ግኝት መሰረት በማድረግ በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአሰራር፣ የአደረጃጀት፣ የሕግና የሥነ ምግባር ብልሹነት ክፍተቶች ካሉ እንዲስተካከሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ምክረ ሃሳብ እንደሚለግሱ አስገንዝበዋል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው በተለይ በምክር የማይስተካከሉ ብልሹ አሰራሮች ካሉ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲሰፍን ግፊት እንደሚያደርግም አክለው ገልጸዋል፡፡

እስካሁን በወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ላይ ክፍተት ያሳዩት ወደ 39 የመንግሥት ተቋማት ላይ ገንዘብ ሚኒስቴር ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ማድረጋቸውንና በተመሳሳይ መልኩ ፍትህ ሚኒስቴርም የወንጀል ምርመራ መጀመሩን ያነሱት ሰብሳቢው፣ በተለይ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሁኔታዎችን ለማረጋጋት ሲባል ፍላጎትን መሰረት ያላደረጉና መመሪያን ያልተከተሉ ግዥን በመፈጸም ለኦዲት የሚያቀርቡበት ሀኔታ መኖሩን አንስተዋል፡፡

በቀረበላቸው ሪፖርትና በምልከታ እንደተገነዘቡት በግዥ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች በጥቅሉ በእውቀትና ግንዛቤ ማነስ፣ በሃላፊነት ጉድለት፣ በሕግ ክፍተት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ክርስቲያን፣ የሕግ ክፍተትና የሃላፊነት ጉድለት ጋር የሚያያዝ ችግር በምክር ቤቱ ጉዳዩን ለሚከታተል ለሌላ ቋሚ ኮሚቴ ሃሳብ እንደሚያቀርቡና የእውቀት ነክ ችግሮችን ደግሞ በተቋማት ሙያዊ ድጋፍ እንዲደረግ ምክረ ሃሳብ እንደሚለግሱ አመልክተዋል፡፡

ባለፈው የምክር ቤቱ ስብሰባ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ከቀረበ በኋላ ከፍተኛ የኦዲት ግኝት የታየባቸው ተቋማትን የመሩ አመራሮች ለአንድ የምርጫ ዘመን ለሦስት ተከታታይ ጊዜያት ምንም አስተያየት የማይሰጥባቸውና በሕይወት ዘመናቸው የህዝብ ሃላፊነት እንዳይሰጣቸው የሚደያርግ አቅጣጫ በቋሚ ኮሚቴው በኩል ቀርቦ ለምክር ቤቱ ቀርቦ መጽደቁን የተናገሩት አቶ ክርስቲያን፣ ይህ ማለት ግን የሕግና የፍትሕ ተቋማት የሕዝብ ገንዘብን የመዘበሩና ያባከኑ አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ አይወስዱም ማለት አይደለም ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውልና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ የአንድ ወገን ሥራ ብቻ ባለመሆኑ የሚዲያ አካላት፣ የፍትሕና ጸጥታ ተቋማትና መላው ሕብረተሰብ የራሱን ድርሻ እንዲያበረከት አቶ ክርስቲያን ጠይቀዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኮራንባችሁ!

ኢትዮጵያ ማህጸኗ ለምለም ነው፡፡ሁልጊዜም ጀግኖችን ያፈራል፡፡ጥንት በአድዋ ለነጻነቷና ለሉአላዊነቷ የተዋደቁላት ጀግኖችን ማህጸኗ እንዳፈራ ሁሉ ዛሬም በአለም አደባባይ ሰንደቅ አላማውን ከፍ የሚያደርጉ ጀግና አትሌቶችን አፍርታለች፡፡

በአሜሪካ ኦሪጎን ሲካሄድ በቆየው 18ኛው የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትጵያውያን የድል አክሊል ተጎናጽፈዋል፡ ፡ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ደምቀው ከርመዋል፡፡በድንቅ አትሌቶች አራት የወርቅ፤አራት የብርና ሁለት የነሃስ ሜዳሌያዎችን በማግኘት ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም ከአሜሪካ በመቀጠል ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቃለች፡፡

በኦሪጎን የተካሄደው 18ኛው የአትሌቲክስ ውድድር ለኢትዮጵያውያን ከውድድርም በላይ ነው፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያውያንን አንገት ዳግም ቀና ያደረገ፤ አሁንም ኢትዮጵያ ፋና ወጊ ሀገር መሆኗን ያሳየ ተጨማሪ ክስተት በመሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን አንድነት መለያቸው፤ማሸነፍ ታሪካቸው መሆኑን፤ ሲተባበሩ የማይደረምሱት ተራራ፣የማያሸንፉት ጠላት፣ የማይወጡት አቀበት እንደማይኖር በተጨባጭ ያሳየ ታሪካዊ አጋጣሚም ነው፡፡

መላው አፍሪካ በቅኝ ግዛት ጨለማ ውስጥ በነበረበት ዘመን ኢትዮጵያውያን በደምና በአጥንታቸው በከፈሉት መስዋዕትነት ለአፍሪካውያን የነጻነትን ችቦ እንደለኮሱት ሁሉ፤ ዛሬም በአለም አቀፉ የአትሌቲክስ ውድድር በአለም መድረክ በመድመቅ ለመላው አፍሪካ የአይበገሬነትን መንፈስ አጋርተዋል፡፡

ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜትና የህዝብ ፍቅር ጠንክሮ መስራት ከተቻለ በብዙ ተግዳሮትና ፈተና ውስጥ አሸንፎ የድል ባለቤት መሆን እንደሚቻል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተጨባጭ ተሞክሮ ለአለም ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

አለም እንደሚያውቀው ባለፉት አራት አመታት ኢትዮጵያውያን በግጭት በተለይም ያለፉትን ሁለት ዓመታት በጦርነት ውስጥ አሳልፈዋል፡፡ የውጭ ጠላቶች እና የውስጥ ባንዳዎች ተቀናጅተው በሚሸርቡት ሴራ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ሁከትና ብጥብጥ ነግሶ ቆይቷል፡፡በርካቶች ከአካባቢያቸው ተፈናቅለዋል፤ሞተዋል፤ተሰደዋል፡፡

ይህ ሁሉ ልብ ሰባሪ ፈተናና ተግዳሮት በስፋት በተስተዋለበት ሀገራዊ እውነታ ውስጥ ፤አትሌቶቻችን ወገባቸውን አጥብቀው በብዙ ድካምና ላብ ፤ ከፍ ባለ ሀገር ወዳድነትና የህዝብ ፍቅር ፤ ሀገርን እንደ ሀገር በአለም አቀፍ መድረክ በድል ከፍታ ማቆም ችለዋል።

የዛሬው አትሌቶቻችን ድል ከቀደሙት ድሎች በላይ በርካታ መልዕክቶችን ያዘለ ነው፡፡ድሉ አትሌቶቻችን የድል ብቻ ሳይሆን የአንድነት፣ የመተሳሰብ እና የመተባበር ተምሳሌት ሆነው በአለም አቀፍ መድረኩ እንዲነግሱ አድርጓቸዋል፡፡

እኛም ኢትዮጵውያን ተባብረን መንቀሳቀስ ከቻልን የትኛውንም ችግር አሸንፈን ፤ተስፋ የምናደርጋቸውን ነገዎች ለመውረስ የተሻለ እድል ሊፈጥርልን እንደሚችል ፤በዚህም በአለም አቀፍ መድረክ ያለንን ገጽታ መቀየር እንደምንችል ትምህርት የሰጠ ነው ።

ከዚህም በላይ ከሁሉም ጥግ የተውጣጡ ኢትዮጵውያን አትሌቶች በፈጠሩት ህብር ኃያላን ሀገራትን ጭምር ድል ነስተው በአለም መድረክ ገዝፈው የመታየታቸው እውነታ፤ የጠላቶቻችን ቅስም የሰበረ እና አንገት ያስደፋ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ልትበታተን ነው፤ አብቅቶላታል የሚል መርዶ ሲነግሩ ለከረሙ ወገኖች ኢትዮጵያ በቀላሉ እንደማትፈርስና ይልቁንም በአለት ላይ እንደተሰራ ቤት መሰረቱ ጠንካራ መሆኑን ያሳየ ነው፡፡ኢትዮጵያዊነት በመከራ ውስጥ የሚጎመራ፤ ኢትዮጵያውያንም መከራና ችግርን ተቋቁመው ለውጤት የሚበቁ ድንቅ ህዝቦች መሆናቸውን ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ ነው፡፡

ድሉ እንደ ሀገር በአሸባሪው ሕወሓት እና ሌሎች አሻባሪ ሀይሎች ፤ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር በቅንጅት በመሆን የከፈቱብንን ጦርነት ከፍ ባለ መስዋእትነት ቀልብሰን ጠባሳው ገና ባላገገመበት ወቅት መሆኑ በራሱ የድሉን ትርጉም ከፍ ያደርገዋል።

አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ከጦርነት ተላቀው በአለም መድረክ መታየታቸው ሁኔታውን በቅርበት ሲከታተል ለነበረ ሁሉ ግርምትን ከመፍጠሩም ባሻገር ኢትዮጵያውያን በፈተና ውስጥ አቅም የሚገነቡ ህዝቦች መሆናቸውን ያሳየ ነው፡፡

ቀደም ባለው ዘመን አባቶቻችን በተለያዩ የጦር አውድማዎች በታላቅ ተጋድሎ ከኛ አልፈው ለጥቁር ህዝቦች ኩራት እንደሆኑ ሁሉ፤ ዛሬም በአሜሪካ ኦሪጎን በተካሄደው 18ኛው የአትሌቲክስ ውድድር ጀግኖች አትሌቶቻችን ከራሳቸው አልፈው ለመላው ጥቁር ህዝብ የኩራት ምንጭ ሆነዋል ፡፡

ዛሬም ከትናንት ልቆ ኢትዮጵያዊነት ደምቋል፡፡ጨለማ የሚመስለው ጊዜ እየሄደ ብርሃን መውጣት ይዟል፡፡ ፊታችን በፈገግታ ፣ ዝማሬያችን በድል ዜማ ደምቋል።አትሌቶቻችንም ዳግም የኩራታችን ምንጭ በመሆናችሁ እኛም ከማንም በላይ ኮራንባችሁ!፡፡

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የአትሌቲክስ ቤተሰቡን ሳቅ የመለሰው ኦሪጎን ድል

ብርሃን ፈይሳ

ታላቁ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ በአንድ ወቅት ይህን ብሎ ነበር፤ «ዓለም እንዲያውቀው የምፈልገው ሃገሬ ኢትዮጵያ በቆራጥነትና በጀግንነት እንደምታሸንፍ ነው»። ይህ አባባል ደግሞ በግብር የታየ በታሪክም የተመዘገበ ሆኖ ዘመናትን ዘልቋል። ቆራጥና ጀግና አትሌቶቿ በጸሃይ ሃሩር በጋለ ጎዳና ባዶ እግራቸውን ደማቸውን እያፈሰሱ ለስሟ ከመሮጥ አልቦዘኑም።

ተደራራቢ ውድድሮች፣ ጉዳትና ድካምም አልበገራቸውም። ህመም፣ ሃዘንና ከወሊድ መልስ ባልጠና አካል ከመሮጥም ወደኋላ አላሉም።ዛሬም ድረስ ራሳቸውን ሳይሆን ሃገራቸውን አስቀድመው ለድሏ፤ ሃገራትን ሁሉ በልጦ ለሚውለበለበው ባንዲራዋና ዓለም ለሚሰማው ብሄራዊ መዝሙሯ ከውድድር አውድ ተሰይመው ለአሸናፊነት ይፋለማሉ።

ሌላኛው ታላቅ አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ «አሸናፊ ለመሆን ሶስት ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ ራስን መግዛት፣ ጠንክሮ መስራት እና ቆራጥነት» እንዳለው፤ እነዚህን ያጣመሩ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከዘመን ዘመን ሃገራቸውን እያኮሩ ይገኛሉ። በኦሊምፒክ፣ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይም እግር በእግር እየተተካኩ በመሮጥ ላይ ናቸው። በድላቸውም ለኢትዮጵያ ክብርን ከመደረብ አልፈው ለህዝባቸውም ደስታን ብቻም ሳይሆን፣ የሃገር ፍቅርን፣ መስዋዕትነትን፣ የዓላማ ጽናትንና አሸናፊነትን ሲያስተምሩ ኖረዋል።

ከሰሞኑ እየሆነ ያለውም ይኸው ነው፤ የዓለም ህዝብ ዓይን፣ ጆሮና ቀልብን በአንድነት በያዘው ውድድር የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ድል አድራጊነት እየታየ ነው።ኢትዮጵያ የዓለም መገናኛ ብዙሃንም የዕለት ዜናቸው ማማሻ፤ የጋዜጦችና መጽሄቶቻቸው አርዕስት ሆናለች። በአሜሪካ ምድር በዩጂን ግዛት ኦሪጎን ከተማ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሜዳሊያ ብዛት ኢትዮጵያ ልዕለ ኃያሊቱን ሃገር አሜሪካንን ተከትላ በሁለተኛነት መቀመጧ ከክብርም በላይ ኩራት የሚሆን ነው።

የድል ዜናው በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የስፖርታዊ ፉክክር ውጤት ከመሆን በዘለለ ትርጉም ያለው ነው።ይኸውም ከወቅታዊው የሃገር ውስጥና እና የውጪ ጫና ጋር በተያያዘ በህዝቡ ስነልቦና ላይ ለደረሰው ህመምም ማስታገሻ በመሆን ላይ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለስፖርት ካለው ልዩ ፍቅር እንዲሁም ከዚህ ቀደም በተለያዩ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ላይ ከተለመደው ስኬት አንጻርም ሳቁን የመለሰ ድል ሆኗል። በተለይ በታላላቆቹ የውድድር አውዶች ኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮናዎች ላይ ይመዘገብ የነበረው የበርካታ ሜዳሊያዎች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ ማሽቆልቆል እያሳየ መምጣቱ አያጠያይቅም።

በዚህም ምክንያት የስፖርት ቤተሰቡ ቅያሜና ጥርጣሬ አድሮበት ሰንብቷል። ስለ ስፖርት ሲል የትኛውንም መስዋዕትነት ለሚከፍለው ህዝብም ይህን የልብ ስብራት ሊጠገን የሚችለው ዳግም ወደ ድል በመመለስ ነውና ኦሪጎን ላይ የተመዘገበው ውጤት ተስፋ ሰጪ ሆኗል።

ስፖርት ለሃገራትና ለዜጎቻቸው የአካላዊና አእምሯዊ ጤና መጠበቂያ ስልት፣ የመዝናኛ አማራጭና የገቢ ማግኛ ዘርፍ ከመሆኑም በላይ ማንነትና መለያ ስለመሆኑ እሙን ነው። የዓለም እግር ኳስን በፕሬዚዳንትነት እየመሩ ያሉት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ እአአ በ2018 ናይጄሪያን ከጎበኙ በኋላ፤ «በናይጄሪያ የእግር ኳስ ስፖርት ፍላጎት ነው ብትሉ ውሸት ነው፤ ምክንያቱም እግር ኳስ ከዚያም በላይ ነው። ፍቅር ወይም እምነት ነው ብትሉም ውሸት ነው፤ ምክንያቱም እግር ኳስ በናይጄሪያ ህይወትም ነው» ማለታቸው ብዙዎችን አነጋግሮ ነበር።

በእርግጥም የፕሬዚዳንቱ ምልከታ ስፖርት ማንነት ስለመሆኑ በግልጽ ያመላከተ ነው። በአፍሪካ ትልቋና የእልፍ ወጣቶች ሃገር ለሆነችው ናይጄሪያ እግር ኳስ አንድ የስፖርት ዓይነት አሊያም የመዝናኛ ዘርፍ ብቻም አይደለም። ይልቁንም ሚሊዮኖች በፍቅር ነገን እያለሙ የሚጫወቱት፣ ለበርካቶች የስራ እድልን የከፈተ፣ ሃገሪቷን በአህጉርና ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ላይ በኩራት እንድትቆም ያስቻለ እንዲሁም የገቢ ምንጭ የሆነም ዘርፍ ነው። እናም ለናይጄሪያዎች እግር ኳስ ህይወት መሆኑ የማያከራክር ነው።

ይህ እውነታ ወደ ምስራቅ አፍሪካ ሲመጣ ደግሞ በአትሌቲክስ ስፖርት የሚገለጥ ነው። ከቀጣናው ሃገራት መካከል አንዷ ለሆነችው ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከስፖርትም በላይ ትርጉም አለው። እንደሃገርም ሆነ እንደህዝብ የማንነት መገለጫና የኩራት ምንጭ ሆኗል። ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ነገር ግን እጅግ በርካታ የሆኑ ወጣቶች ነገን አሻግረው እየተመለከቱ ይሮጣሉ። ተስፋቸው በአትሌቲክስ ላይ የተመሰረተ ነው፤ የትኛውንም መስዋዕትነት ከመክፈል ወደኋላ አይሉም። ሲሳካላቸው ደግሞ በገንዘባቸው ሃገራቸውንና ህዝባቸውን ከማገልገል ወደኋላ አይመለሱም።

ኦሪጎን ላይ የታየው የአትሌቶቻችን ጀግንነትና ብርታትም ምንጩ ይኸው የሃገርና የህዝባቸው ፍቅር ነው።ከዚህ ቀደም የደረሰባቸው መጉላላት፣ ዕድልና ትኩረት ማጣት፣ ከቤተሰብና ከወዳጅ መራቅ፣... ቅንጣት ታህል ቅሬታ ሳያሳድርባቸው ሃገራቸውን ወደማገልገል መመለሳቸው በእርግጥም ለሃገራቸው ያላቸውን ጽኑ ፍቅር የሚያሳይ ነው። ከዓመት በፊት በቶኪዮ ኦሊምፒክ የተከሰተውና የስፖርት ቤተሰቡንም አንገት ያስደፋው አሳፋሪ ችግር በዚህ ውድድር ተሽሯል።

ይህ ለስፖርት ቤተሰቡ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ከመሆኑ ባለፈ እየተገኙ ያሉ ውጤቶችም በአዳዲስ ርቀቶች የተስፋ ጭላንጭል ያስመለከተ ሆኗል። እንደ 3ሺ መሰናክል ባሉ ርቀቶች ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ውስጥ መግባትና ከጠንካራ ተፎካካሪዎች ተርታ መሰለፍ ሌሎች የስኬት መንገዶችን አመላካችና የአብዮት ጅማሬ ማሳያም ሆነዋል።

አስደሳች ከሆነው ድል በተቃራኒ ቀድሞ በምንታወቅባቸው የመም ላይ ረጅም ርቀት ውድድሮች የታየው ሁኔታ በአትሌቲክስ ቤተሰቡ ላይ ጥርጣሬን የጫረ መሆኑም መታለፍ የለበትም። ከማርሽ ለዋጩ ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር የኦሊምፒክ ድል አንስቶ እስከ 2020(እአአ) ቶኪዮ ኦሊምፒክ ድረስ የዘለቀው የ10ሺ ሜትር የወንዶች ድል፤ ኦሪጎን ላይ መነጠቁ ያስቆጫል።

በርቀቱ የተካፈሉ አትሌቶች ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረጋቸው እሙን ቢሆንም ከዓመት ዓመት ተወዳዳሪን ሳይለዩ በተመሳሳይ የአሯሯጥ ስልት መገኘት ዋጋ ማስከፈሉ አይቀርምና ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# ወደ መጠጥ ቤትነት ተቀይሮ የቆየውን ትምህርት ቤት የማስመለስ ትግል

**ሙሉቀን ታደገ**

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል «ፍረዱኝ» የተሰኘው የምርመራ አምድ በየሁለት ሳምንቱ እየተዘጋጀ እንደሚቀርብ ይታወቃል። በዚሁ አምድ ከሁለት ሳምንት በፊት «ለመጠጥ ቤት የዋለው ትምህርት ቤት» በሚል ርዕስ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት የተፈጠረውን ውዝግብ መነሻ በማድረግ አንድ የምርመራ ዘገባ መስራታችን ይታወሳል። የዛሬው ዝግጅታችንም ከባለፈው የቀጠለ ምርመራን ይዳስሳል።

ለዛሬው ዝግጅታችን መነሻ ይሆን ዘንድ ከባለፈው የምርመራ ዘገባችን የተወሰነውን በወፍ በረር እናስቃኛችሁ። በደል ተፈጽሞብናል ሲሉ አቤቱታ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኙት ህጻን አለም አጸደ ህጻናት እና አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት መምህራን ናቸው። «በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኘው የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር በ2004 ዓ.ም ከመንግስት በአደራ የተረከባቸው ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነውን ህጻን አለም አጸደ ህጻናት ማስተማሪያ ህንጻ ወደ መጠጥ ቤት በመቀየር ተማሪዎችን ከመበተኑ ባለፈ መምህራንንም ለአልተጋባ እንግልት ዳርጎናል። ይሄው ሸማች ማህበር በአደራ የተረከበውን የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት የሚያስተምሩ መምህራንን ጥቅማ ጥቅም በመከልከል እና መምህራንን አሰላችቶ ትምህርት ቤቱን ለቀው እንዲሄዱ በማድረግ የትምህርት ቤቱን ህንጻ ለግል ጥቅም ለማዋል በማሰብ በደል እየፈጸሙብን ነው»ሲሉ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት ማለታቸውን እና የኢትዮጵያ ህዝብም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ፍርድ ይሰጥ ማለታችን ይታወቃል።

ከትምህርት ቤቶቹ አቤቱታ ያቀረቡ መምህራን በርካታ ናቸው። ይሁን እንጂ የሁሉም መምህራን አቤቱታ አንድ አይነት ስለሆነ ህጻን አለምን እና አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናትን የሚወክሉልን ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች አንድ፣ አንድ መምህራን መርጠን ቃለ ምልልስ አድርገናል። ለቃለ ምልልሱ የተመረጡት መምህራን በትምህርት ቤቶቹ ከፍተኛ የማስተማር ልምድ ያላቸው እንደነበሩ አስታውሰን አልፈናል።

ከመምህራኖቹ በተጨማሪ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት በሚገኙ ሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጠሩ ከተባሉ ችግሮች ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአራዳ ሸማቾች ህብረት ስራ ኃላፊ ጋር ቃለ ምልልሶችን አድርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ ቀኙን አይቶ የራሱን ፍርድ መፍረድ ይችል ዘንድ የአራዳ ክፍለ ከተማ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር ኃላፊውን ስለትምህርት ቤቶቹ ምን ያውቃሉ? ሲል ላቀረበው ጥያቄ የህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ጀማል እስማኤል ምላሽ ሰጥተዋል።

አቶ ጀማል እንደሚናገሩት፤ አሁን በኃላፊነት ወደሚሰሩበት ጽህፈት ቤት ከመጡ ቅርብ ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ ከህጻን አለም አጸደ ህጻናት እና ከአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ሶስት ወራት ያህል መረጃዎችን በማሰባሰብ ስለጉዳዩ ከፍተኛ ክትትል እና ጥናት ሲያደርጉ ነበር። በጥናታቸውም የህጻን አለም ትምህር ቤት እና የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤቶች ለበርካታ ዓመታት የትምህርት አገልግሎት ሲሰጡ መቆየታቸውን አረጋግጠዋል።

እንደ አቶ ጀማል ገለጻ ፤ ለህጻን አለም አጸደ ህጻናት ተማሪዎች ትምህርት ይሰጥበት የነበረው ቤት በከተማ አስተዳደሩ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ በቅርስነት የተመዘገበ እና በከተማ አስተዳደሩ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ አማካኝነት እድሳት ተደርጎለታል። ይሁን እንጂ ከእድሳት በኋላ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው ቤቱ የመማር ማስተማር አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑን እና በቀጣይም ቤቱ ለምን ሊውል እንደሚችል የምንገልጽላችሁ ይሆናል የሚል ደብዳቤ ትምህርት ቤቶቹን በአደራ ለሚያስተዳድረው የሸማች ማህበር ተልኳል።



የሕፃን ዓለም አፀደ ሕፃናት ከፊል ገፅታ

ትምህርት ቤቱ እድሳት ከተደረገለት በኋላ ለረጅም ጊዜ ተዘግቶ ቆየ። ለምን አገልግሎት መዋል እንደሚችል እንደሚያሳውቋቸው ተገልጾ የነበረ ቢሆንም ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ስለጉዳዩ ምንም ሳይል ለእረጅም ጊዜ በመቀመጡ ቤቱ ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመከሩት የሸማቾች ቦርድ አመራሮች ቤቱን መዝናኛ ክበብ ለማድረግ ውሳኔ ወሰኑ።

ይህ በእንዲህ እያለ የአራዳ ክፍለ ከተማ ባህል እና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት በ2012 ዓ.ም እና 2013 ዓ.ም በጻፋቸው ደብዳቤዎች ለዘመናት ትምህርት ሲሰጥበት የነበረውን ቤት የቅርስ ቤት ስለሆነ እና ትምህርት ቢሰጥበት ለጉዳት ሊዳርግ ስለሚችል ቤቱን ልታስረክቡን ይገባል ሲል ለሸማቾች ደብዳቤ ጻፈ። ይህን ተከትሎም ‹‹ቤቱን የባህል እና ቱሪዝም አላስረከበንም ! ቤቱን ባህል እና ቱሪዝም ስላደሰው ብቻ ቤቱን የእሱ ብቻ አድርጎ ሊመለከት አይገባውም። ሊሆንም አይችልም። እነኝህን ቤቶች መንግስት ተጠያቂነት በሚያስከትሉ ሰነዶች በአደራ ሸማቾች እንዲያስተዳድራቸው የተሰጡ ናቸው›› የሚል ምላሽ መስጠታቸውን አቶ ጀማል ይናገራሉ ።

ይህን የሸማቾች ቦርድን ምላሽ የሰማው ባህል እና ቱሪዝም ስለቤቱ ይህን ነው የሚባል አቅጣጫ ጠቋሚ ደብዳቤ ከመስጠት ተቆጥቦ ወራት ተቆጠሩ። ከባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ምንም ምላሽ ያጡት የሸማች ቦርድ አመራሮች ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሁነኛ መፍትሄ እስከሚሰጠው ድረስ ቤቱን ወደ መጠጥ ቤት እንዲዞር አደረጉ። ይህን ተከትሎ በፌስ ቡክ እና መሰል ማህበራዊ ሚዲያዎች ትምህርት ቤት ወደ መጠጥ ቤት ተቀየረ፤ ትውልድ እየተገደለ ነው እና መሰል አስተያየቶች ይሰራጭ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአራዳ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ማህበር ጽህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ጀማል ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ለማፈላለግ ትምህርት ቤቱን መጠጥ ቤት እንዲሆን የወሰኑትን የሸማች ማህበር አመራሮች ፣የአራዳ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽህፈት ቤት እና የባህል እና ቱሪዝም ኃላፊዎች ፣የወረዳ ስድስት የወተመህ( ወላጅ ፣ ተማሪዎች እና መምህራን ህብረት) እና የትምህር ቤቱ መምህራን ባሉበት ውይይት ማድረጋቸውን ይናገራሉ።

በውይይቱም ቦርዱን ለምን ትምህርት ቤቱን ወደ መዝናኛ ክበብነት እንደቀየሩት ተጠየቁ። ከውይይቱ ተሳታፊዎች የቀረበላቸውን ጥያቄ ምላሽ የሰጡት የሸማቾች ቦርድ አመራሮች ፤ የአዲስ አባባ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ከእድሳት በኋላ ‹‹ቤቱ ለትምህርት ቤት እንዳይውል፤ ቤቱ ለምን መዋል እንዳለበት እስከምናሳውቃችሁ ድረስ ለትምህርት እንዳትጠቀሙት የሚለውን የውሳኔ ደብዳቤ አሳዩ። የሸማቾች ቦርድ አመራሮች አያይዘውም ቤቱን ለትምህርት ቤት አውሉት የሚባል ከሆነ ቤቱን ለትምህርት ቤት ለማዋል ሁለት ጊዜም ማሰብ አይፈልግም። ነገር ግን ባህል እና ቱሪዝም ተማሪዎች ቤቱ ላይ ጉዳት ሊያደርሱበት ስለሚችሉ ቤቱን አስረክቡን የሚለው ነገር እኛ ቤቱን ከህዝብ እና ከመንግስት እስከተረከብነው ድረስ ቤቱን ለባህል እና ቱሪዝም አናስረክብም።›› ሲሉ በውይይቱ ላይ አቋማቸውን መግለጻቸውን ይናገራሉ። በዚህም ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱ ወደ ትምህር ቤት እንደሚቀየር የጋራ መግባባት ላይ ተደረሰ።

ይህ ሲሆን የባህል እና ቱሪዝምን ደብዳቤ ተላልፈን አይደለም የሚሉት የህብረት ስራ ኃላፊው፤ ነገር ግን በባህል እና ቱሪዝም ቤቱ ለመማር ማስተማር አይሆንም የተባለበት በቂ አሳማኝ ምክንያት ስላልነበረ ነው ይላሉ። ምክንያቱም ይህ ውዝግብ የተነሳበት ቤት ሸማቾች ሳይረከበው በፊት ለበርካታ ዓመታት የመማር ማስተማር አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል። የሚማሩት ተማሪዎችም የአጸደ ህጻናት ተማሪዎች ስለሆኑ በቅርሱ ላይ አደጋ ያደርሱበታል የሚል አሳማኝ ግምገማ አላገኘንም። በዚህ ምክንያት ቤቱ ትምህርት ቤት ሆኖ መቀጠል አለበት። ትምህርት ቤት የነበረን ቤት መዝናኛ ክበብ ማድረግ ፍጹም ተገቢ ያልሆነ እና አግባብነት የሌለው ነገር ነው የሚል የጋራ መግባባት ላይ ተደረሰ። ይህ ውሳኔ የተወሰነው ቀድሞ ከነበሩ ቦርዶች ጋር መሆኑን አቶ ጀማል አመላክተዋል።

ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም የመጠጥ ቤቱን ለመዝጋት ስምምነት ላይ ከተደረሰ እስካዛሬ ለምን የመጠጥ መሸጥ ስራው አልተቋረጠም? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ጠይቋል። ለተጠየቁት ምላሽ የሰጡት አቶ ጀማል እንደተናገሩት ፤ ቤቱ ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከመጠጥ ቤት ወደ ትምህርት ቤት እንዲቀየር ውሳኔ የታላለፈ ቢሆንም ውሳኔው ከተላለፈ ማግስት በ2014 ዓ.ም የበጀት አመት አጋማሽ በኋላ በወረዳ ስድስት የሸማቾች ጠቅላላ ጉባኤ ነበር። በዚያ ጠቅላላ ጉባኤ ውስጥ የአመራር ለውጦች ተደርገዋል። የሸማቾች አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመናቸውን ጨርሰው በአዲስ ስለተተኩ ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ይዘጋል የተባለው የመዝናኛ ክበብ በተባለው ቀን መዘጋት አልቻለም። የሸማቾች የአመራር ለውጥ ለሐምሌ አንድ የተባለውን ውሳኔ አስተጓጉለዋል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ይሁን እንጂ ቤቱን ለ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን አገልግሎት እንዲሰጥ በሚል እቅዶች ታቅደው ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው። በሚቀጥለው ዓመት የትምህርት ስራውን ለማስጀመር ታቅደው ከነበሩት እቅዶች መካከል አንዳንዶቹ መሬት ላይ ወርደው መተግበር መጀመራቸውን ይገልጻሉ። ከመጪው አመት ትምህርት ጋር ተያይዞ ሸማቾች የአቅም ውስንነት እንዳያጋጥማቸው እና ትምህርት ቤቶችን በሚፈለገው ልክ የመማር ማስተማር ስራቸውን እንዲጀምሩ ለማድረግ የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤትም የራሱን ድጋፍ ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሷል ይላሉ።

በእርግጠኝነት ከሐምሌ 18 ቀን 2014 ጀምሮ ለመዝናኛ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው ቤት ተዘግቶ የትምህርት ስራውን ለማከናወን የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ይጀምራል። አሁን ላይ የቅድመ ዝግጅት ስራ ተጀምሯል የሚለውን እንድትይዙልኝ እፈልጋለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናትን በተመለከተ በትምህርት ሪጉላቶሪ ኤጀንሲ ግምገማ መሰረት ትምህርት ቤቱ ትምህርት ለመስጠት የሚችልበት ደረጃ አነስተኛ ነው። ትምህርት ቤቱ በሪጉላቶሪ ኤጀንሲ የተቀመጡ በርካታ መስፈርቶችን አያሟላም። ይህ በትምህርት ሪጉላቶሪ ኤጀንሲ የተወሰነው ውሳኔ እውነት ነው። ትምህርት ቤቱ በትምህርት ሪጉላቶሪ ኤጀንሲ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟላቸው ነገሮች አሉት። ለምሳሌ ከተማሪዎች እና ክፍል ጥምርታ አንጻር ሲታይ ለእድሳት የተዘጋው የህጻን አለም አጸደ ህጻናት ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ወደ አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ሄደው እንዲማሩ በመደረጉ በአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት በአንድ ክፍል ውስጥ መማር ከነበረበት የተማሪዎች ብዛት በላይ እየተማሩ ነው። ይህ የተማሪዎች ክፍል ጥምርታ በሪጉላቶሪ ኤጀንሲ ግምገማ ከበቂ በታች ነው። ከዚህ በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ ሜዳ አቧራ በመሆኑ ለህጻናት መጫወቻ የማይመች ነው። ይሄም በሪጉላቶሪ ኤጀንሲ ግምገማ ከበቂ በታች ነው።

ስለሆነም እነኝህን እና መሰል በትምህርት ቤቱ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሰራ ነው ። ይሁን እንጂ ከትምህርት ቤቶቹ አጠቃላይ ችግሮች ጋር ተያይዞ የመምህራን እና ወላጆች የሸማቾች ቦርድ ትምህርት ቤቱን ለመንግስት ይስጥ የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። ለዚህም እንደዋነኛ ምክንያት ያነሱት ቦርዱ በራሱ የተፈጠሩ ችግሮችን መፍታት ስላማይችል የሚል ነው።


ከዚህ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የማህበሩ ቦርድ አባላት አቋም ከመምህራን እና ወላጆች ጥያቄ እና ፍላጎት ጋር የተለያየ ነው። ይሁን እንጂ የማህበር አመራር ቦርዱ «እኛ በራሳችን ማስተዳደር እንችላለን» ያሉ ሲሆን፤ አስተዳድሩም ወይም ታስተዳድራላችሁ ብሎ መወሰን ያለበት መምህራን ሳይሆኑ ጠቅላላ ጉባኤው ነው ሲል የሸማቾች ቦርድ አመራር አባላት መከራከራቸውን አቶ ጀማል ያስረዳሉ።

በትምህርት ቤቶች የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሸማቾች ቦርድ ቃል ገብቷል የሚሉት አቶ ጀማል፤ ችግሮችን መፍታት የማይችሉ ከሆነ ጠቅላላ ጉባኤው በሚወስነው መሰረት ትምህር ቤቱን ለመንግስት እንደሚያስረክቡ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ በ2015 ዓ.ም የበጀት አመት ከፍተኛ በጀት በመበጀት ሸማቾች የነበሩባቸውን ጉድለቶች ቀርፎ የመማር ማስተማር ስራውን ለማስሄድ ስራ መጀመራቸውን አቶ ጀማል አመላክተዋል።

ሌላው የሚነሳው የመምህራን የደመወዝ ጥያቄ ነው ። 30 ዓመት ሰርተን የሚከፈለን ገንዘብ ዘመኑን ያላገናዘበ እና በጣም አነስተኛ ነው የሚል ሰፋ ያለ የመምህራን እና ሰራተኞች እሮሮ ነበር። ይህ የተፈጠረው ደግሞ ቦርዶች ስለሚቀያየሩ መሆኑን መምህሩ አቶ ጀማል ያስረዳሉ።

በዚህ አግባብ የመምህራንን ደመወዝ ለማሻሻል በሚል የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለመምህራን ምን ያህል ይከፍላሉ? የሚለውን ለማጣራት እና ሸማቾችም ለመምህራኑ በመንግስት መምህራን ልክ ለመክፈል የመንግስት መምህራን ደመወዝ ስኬል ከትምህርት ጽህፈት ቤት ወስደናል። በዚያ ልክ ደመወዛቸውን ለማሻሻል እየሰራን ነው። ትምህርት ቤቱ ምን ያህል ገቢ ያስገኛል የሚለውንም ትንታኔ ሰርተናል። ከትምህርት ቤቶች የሚገኘው ገቢ አነስተኛ ቢሆንም እንኳን ሸማቾች ማህበር ከሌሎች የሸማቾች ማህበራት ከሚያገኛቸው ገቢዎች ትምህርት ቤቶችን በመደጎም እንደ ማህበር ለሃገራቸው ማበርከት የነበረባቸውን ማህበራዊ ሃላፊነቶች መወጣት እንዳለባቸው ስምምነት ላይ ተድርሷል ይላሉ።

# ተጠየቅ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፤ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ
Addis Ababa City Government Culture, Arts and Tourism Bureau

ቁጥር:
Ref. No
ቀን:
Date

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለወረዳ 6 አንድነት ቀበሌ 11/12 ሽማች ህዝብ ሥራ ማህበር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤት ጥገናና እድሳት ሥራ መጠናቀቁን ስለመግለፅ

የአዲስ አበባ ባህል፤ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤትን በጀት በመመደብ ጥገናና እድሳት እንዲያገኝ ማድረጉ ይታወቃል። ታሪካዊ ቅርስ ቤቱ በቢሮውና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ እየተደረገለት የጥገና ስራው በባለሙያዎቹ ተረጋግጦ በመጠናቀቁ የሳይት ርክክብም የጥገና ስራ ሲያከናውን ከነበረው ተመስ እና ብርሃን ኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር ተፈፅሟል።

በመሆኑም የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤት ቀድሞ ይሰጥ የነበረውን የመማርያ አገልግሎት ለቅርሱ ደህንነትና ጥበቃ ለመማርያ ተግባር መዋል ስለማይገባው ቅርሶች ተጠግነውና እንክብካቤ ተደርጎላቸው የቅርስ አዋጁ በሚያስቀምጠው አገልግሎት ላይ ብቻ መዋል ስለሚገባቸው የከተማ አስተዳደሩ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ በማንና ለምን አገልግሎት መዋል እንደሚገባው እስከሚገለፅ ድረስ እንድትጠብቁ ስንል እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ
- ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን
- ለአራዳ ክፍለ ከተማ ባህል፤ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ጽ/ቤት
- ለህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ት/ቤት
- ለባህል ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ
- ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት

አዲስ አበባ

Tel. 0111264425/0111264405
Fax: 0111264614
Email: info@addisculture tourism.g
Webite:WWW.addisculture tourism g

**ስመጠጥ ቤት የዋለው ትምህርት ቤት እስከ ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ወደ ቀድሞ ስራው እንዲመለስ ከክፍለ ከተማው ሸማች ማህበር ጋር መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ አሁን ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ጽህፈት ቤት የማይሰጡ ከሆነ ሸማቾች በቀጣዩ የትምህርት ዘመን እፈታቸዋለሁ ያላቸውን ችግሮች በቋሚነት መፍታት አይቻልም**

በዚህም የመምህራን ጥያቄዎች አግባብነት ያላው በመሆኑ በትክክለኛው መንገድ ይስተናገዳልየሚሉት አቶ ጀማል ፤ ትምህርት ቤቶችም የሬጉላቶሪ ኤጀንሲ የሚጠይቀውን መስፈርት እንዲያሟሉ የሚደረግበትን አግባብ ከፍተኛ የሆነ አትኩሮት ሰጥተው ድጋፍ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ለመፍጠር በጠቅላላ ጉባኤ ጉባኤተኛው እንዲወስን ተድርጓል ይላሉ። ትምህርት ቤቱ ትምህርት ቤት ሆኖ እንዲቀጥል ከ2015 ዓ.ም በፊት አስፈላጊው እድሳት እንዲደረግለት ውሳኔ መወሰኑን ጠቁመዋል። ትምህርት ቤቶችን ለማሳደስ እና ለማሟላት ያለባቸውን ግብዓቶች ለማሟላት ቦርዱ የራሱን ውሳኔ አስተላልፎ ጨረታ ለማውጣት በሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ለክፍለ ከተማው ህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ጋር በመነጋገር ስራዎች ተጀምሯል ብለዋል።

ከደመወዝ ጋር ተያይዞ ባለሙያዎች ተመድበው ክትትል እያደረጉ መሆናቸውን ይናገራሉ። ተገቢው ደመወዝ የማይከፈለው መምህር ተገቢውን እውቀት ለህፃናት ይሰጣል ተብሎ እንደማይታመን መግባባት ላይ መደረሱን አቶ ጀማል ይናገራሉ።

እንደ አቶ ጀማል ገለጻ፤ የሸማች ማህበራት የሚያስተዳድሯቸው ትምህርት ቤቶች የሚቆጠሩት እንደ ግል ትምህርት ቤቶች ነው። እንደ ግል ትምህርት ቤት የሚቆጠር ስለሆነ ብቻ ግን ወላጆች ለትምህርት የሚከፍሉት ዋጋ የተጋነነ አይደለም። የወላጆችን የመክፈል አቅም ያማከለ ነው።ምክንያቱም የሸማች ማህበራት አንዱ እና ዋነኛ ተግባር የሀገሪቱን ገበያ ማረጋጋት ስለሆነ ክፍያው ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

‹‹በመጪው የትምህርት ዘመን በሁለቱም ተቋማት የሚነሱ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየሰራን ነው። በእርግጠኝነትም አሁን ባሉን ቀሪ ወራቶች ተዘጋጅተን እነኝህን ችግሮች እንደምንፈታ እና በቀጣይ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ጥሩ ቁመና ያለው ትምህርት እንደምናስጀምር እርግጠኛ ነን›› ሲሉ ተናግረዋል።

ከጅምሩ ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን በአደራ መቀበል ነበረበት ወይ ? ለመቀበልስ የሚያስችል መመሪያ አለ ወይ ? እርስዎስ ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን በአደራ መቀበሉን ያምኑበታል ወይ? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቶ ጀማልን ጠይቋል።

ዝግጅት ክፍሉ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት አቶ ጀማል እንደገለጹት፤ ከአለም አቀፍ እና ከሃገር አቀፍ ተሞክሮ አንጻር የህብረት ስራ ማህበራት እንደዚህ አይነት ስራዎችን ይሰራሉ። በእኛ ሃገር የህብረት ስራ ማህበራት መስራት ከሚገባቸው ገበያን ከማረጋጋት አንጻር እና በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ማበርከት ከሚገባቸው ሚና አንጻር እየሠሩ ያሉት በጣም ጥቂት ስራ ነው። በአጠቃላይ የህብረት ስራ ማህበራት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ 15 በመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ይፈለጋል። ነገር ግን አሁን ላይ በዚያ ደረጃ ላይ አይደሉም።

በሌሎች ሀገራት ላይ የህብረት ስራ ማህበራት ጤና ጣቢያ ፣ ሆስፒታሎች ጭምሮ ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማትን ያስተዳድራሉ። ስለዚህ ለህብረት ስራ ማህበሩ ትምህርት ቤቶች በአደራ መሰጠቱ ተገቢ ነው ብለው እንደሚያምኑበት ይናገራሉ። ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ለሸማቾች በአደራነት የተሰጡት በአራዳ ክፍለ ከተማ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ በቦሌ ክፍለ ከተማ የሚገኝ አንድ ጤና ጣቢያ ለሸማቾች ተሰጥቷል። በሌሎች ክፍለ ከተሞች ላይ በተመሳሳይ ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች ተሰጥተዋል። በአራዳ ክፍለ ከተማ ችግር ከተፈጠረባቸው ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች በአደራ ተሰጥተዋል። ስለሆነም ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች መሰጠቱ ብዙ የሚያነጋግር አይደለም ብለዋል።

ሁላችንም የምንዳኘው በሃገሪቱ ህጎች እና መመሪያዎች ነው። በመሆኑም በምን መመሪያ እና ህግ ተመስርቶ ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች ተሰጡ? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት አቶ ጀማል የጠየቀ ሲሆን፤ አቶ ጀማል በሰጡት ምላሽ፤ በወቅቱ እርሳቸው ስላልነበሩ ትምህርት ቤቱ ለሸማቾች የተሰጠበትን መመሪያ መናገር ባይችሉም ትምህርት ቤቶችን ለመቀበል ግን ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ሰነዶችን ከመንግስት ጋር መፈራረማቸውን ይናገራሉ።

መምህራን እና ወላጆች በሸማቾች በአደራ በመሰጠታቸው የሚያነሷቸው ቅሬታዎች አሉ። ለምሳሌ የመንግስት መምህራን ከደመዛቸው ባሻገር የትራንስፖርት የሰርቪስ አገልግሎት ይሰጣቸዋል። የቤት አበልም ይከፈላቸዋል። ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችም አሉ። በህዝብ ትምህርት ቤት የሚማሩ ህጻናት ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ ወላጆች የሚያስተምሩበት ነው። እነዚህን እንዴት ልታሟሉ አስባችኋል? እነኝህ ወላጆች ትምህርት ቤቱ ወደ መንግስት ዞሮ ቢሆን ኖሮ ልጆቻቸው የምገባ እና መሰል ጥቅማ ጥቅሞችን ያገኙ ነበር። እናንተ እነኒህን ጥቅማ ጥቅሞች ለማማሏት ምን እየሰራችሁ ነው? ሲል ዝግጅት ክፍሉ አቶ ጀማልን ጠይቆ ነበር።

ለጥያቄው ምላሽ የሰጡት አቶ ጀማል እንዳመለከቱት፤በእነኝህ ትምህርት ቤቶች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ ሰዎች የኑሮ ደረጃቸው አነስተኛ ነው። በዚህም ልጆቻቸው በመንግስት ትምህርት ቤት ቢማሩ ኖሮ ከመንግስት የሚሰጣቸው ደብተር ፣ ዩኒፎርም እና የምገባ ተጠቃሚ ይሆኑ ነበር። ከክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ጋር በተወያዩበት ጊዜ የትምህርት ጽህፈት ቤቱ አንድ የወሰደው ኃላፊነት እንደነበር ተናግረዋል። አቅም በፈቀደው መጠን ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚበጀቱ በጀቶች በተለያዩ ምክንያት የሚተርፉ በጀቶችን ለእነኝህ ትምህርት ቤቶች ድጋፍ ለማድረግ እንደሚችል የገለፀላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

ስለዚህ ከምገባ አንጻር ተማሪዎችን ለመመገብ የሚያስችሉ እድሎች ዝግ ናቸው ብለው እንደማያምኑ የተናገሩት አቶ ጀማል፤ ነገር ግን ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን በአደራ እንደተቀበለ አካል የተለያዩ ተቋማትን በማስተባበር ከምገባ ውጪ ያሉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማለትም ዩኒፎርም ፣ ደብተር፣ የመሳሰሉት ለመንግስት ተማሪዎች በሚደረጉ ድጋፍ ልክ ለሁለቱ አጸደ ህጻናት ተማሪዎችም ድጋፍ ይደረጋል። በአደራ ለምታስተዳድሯቸው ትምህርት ቤቶች ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለይቶ ለመርዳት የሚከብድ አለመሆኑን ጠቁመዋል።

ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን መቼ እና እንዴት ለመንግስት ሊያስረክብ ይችላል? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቶ ጀማልን ጠይቆ ነበር። ትምህርት ቤቶችን ለማስረከብ አሳማኝ ምክንያት እስካለ ድረስ የሸማች ማህበሩ ትምህርት ቤቶችን ለትምህርት ቢሮ የማያስረክብበት አግባብ አይኖርም። አሁን ላይ ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን ማስተዳደር አለበት የሚለው የመጀመሪያ አማራጭ አይደለም። ነገር ግን ሸማቾች ያሉበትን ችግር ቀርፎ መንግስትን የሚደግፈበት አግባብ ከተፈጠረ የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ሸማቾችን የመደገፍ አቋም አለው ሲሉ መናገራቸውን ተከትሎ የዝግጅት ክፍሉ ወደ አራዳ ክፍለ ከተማ ትምህርት ፅሕፈት ቤት አምርቷል።

## የአራዳ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ምላሽ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት በሚገኙ ሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጠሩ ከተባሉ ችግሮች ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለአራዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ የአጸደ ህጻናቱ ለሸማቾች ማህበር መሰጠት ነበረበት ብለው ያምናሉ ? ትምህርት ቤቶቹ ሲሰጡ የትኛውን መመሪያ መሰረት ተደርጎ ነው የተሰጡት ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ የህጻን አለም ትምህርት ቤት እንደሌሎች የግል ተቋማት በ1966 ተወርሷል ያሉት አቶ ወንድሙ ፤ እነኝህ በአዋጅ የተወረሱ ትምህርት ቤቶች የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሆነው ነበር። በህዝብ ትምህርት ቤትነት ሲተዳደሩ ከቆዩ በኋላ በ2003 ዓ.ም የህዝብ ትምህርት ቤቶች በህዝብ ጥያቄ መሰረት በመንግስት እንዲተዳደሩ ሆነ። ይሁን እንጂ በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች በአደራነት መሰጠታቸውን ይናገራሉ።

በ2003 ዓ.ም ትምህርት ቤቶች ለሸማቾት የተሰጡበትን ሂደት ለማጣራት መሞከራውን የተናገሩት አቶ ወንደሙ፤ ለሸማቾች የተሰጠበት አግባብ መሰረታዊ ችግር ያለበት መሆኑን መገምገማቸውን ይናገራሉ። በመሆኑም ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች የተሰጡበት አግባብ መመሪያዎችን የሚጣረስ እና ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ተናግረዋል።

ከመመሪያ ውጪ ከሆነ ትምህርት ቤቶች ለሸማቾች የተሰጡት ትምህርት ጽህፈት ቤት ትምህርት ቤቶችን ለማስመለስ ምን እየሰራ ነው? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የጠየቃቸው አቶ ወንድሙ ፤ትምህርት ቤቶችን ለማስመለስ እስከ አሁኗ ሰዓት ደረስ ከፍተኛ ትግል እያደረጉ መሆናቸውን አመላክተዋል።

ለመጠጥ ቤት የዋለው ትምህርት ቤት እስከ ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ወደ ቀድሞ ስራው እንዲመለስ ከክፍለ ከተማው ሸማች ማህበር ጋር መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ አሁን ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ጽህፈት ቤት የማይሰጡ ከሆነ ሸማቾች በቀጣዩ የትምህርት ዘመን እፈታቸዋለሁ ያላቸውን ችግሮች በቋሚነት መፍታት አይቻልም ሲሉ አመላክተዋል። በመሆኑም በእርሳቸው እምነት በፖለቲካዊ ውሰኔ ተወስኖ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቢሮ ሊመለሱ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# "ሰማይ ይታረሳል…!"

### የጉዳያችን ማዋዣ፡- "በልሃ ልበልሃ!"

የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ የፍትሕ አካሄድ ሥርዓት እንደዛሬው እንዳልነበረ "ጥንታዊነቱ" ራሱ ለራሱ መልስ ይሰጣል። እርግጥ ነው፤ ዛሬን ከትናንት ጋር ማነጻጸሩ አግባብ ያለመሆኑ ባይጠፋንም አንዳንዴ ግን "አምሳያ ገጠመኞችን" ስናስተውልና ያለፉትን ዓመታት በአርምሞ ስንቃኝ ትናንት ትዝ እያለን ብንቀዝዝ "የነበር ምርኮኞች" አሰኝቶ ሊያስነቅፈን አይገባም። ደግሞስ የትናንትን የጉዞ አሻራ (ፈለግ) በማስታወስ የዛሬውን እርምጃችንን ብንመረምርና "የእድገታችንን" ቁመት ብንፈትሽበት ምን ክፋት ይኖረዋል?

የጥንታዊው የበልሃ ልበልሃ የሙግት አካሄድና ሥርዓት እንደ ዛሬው ዳኝነት በተደራጀ አዳራሽ ውስጥ ዋናዎቹ ፈራጆች ከፍ ባለ ሞገሳማ መንበር ላይ ተሰይመውና ጥቁር ካባ ደርበው፣ ዐቃቤ ሕጉና ጠበቃውም ግራና ቀኝ ቆመው፣ ከሳሽና ተከሳሽ አንገታቸውን ዘልሰውና እጃቸውን አጣምረው፣ የጸጥታ ሠራተኞችም አጥር ሆነው ማስረጃ እየተጎለጎለና ምስክሮች እየተነተኑ የሚፋለሙበት ዓይነት የሙግት አካሄድ አልነበረም።

ለሙግቱ መፋለሚያ የሚመረጠው ቦታ የዛፍ ጥላ ወይንም አውላላ ሜዳ ሆኖ ተመልካች ዙሪያውን ከቦ የሚያዳምቅበት ትዕይንት ነበር። ተሟጋቾቹም ሆኑ ተመልካቹ እንደ ዛሬው የፍርድ ቤት ሥነ ሥርዓት "ኮፍያህን አውልቅ፣ ያጣመርከውን እግር ዘርጋ፣ የተዝናኖት አቀማመጥሽን አስተካክይ፣ ከሹክሹክታ ታቀቡ ወዘተ." ከሚሉ የማስፈራሪያ ትብታቦች በእጅጉ የጸዳ ነበር።

ይልቅስ፤ "ተውኔታዊ ባሕርይ የነበረው የከሳሽና የተከሳሽ አለባበስ፣ አቋቋም፣ ዘንግ አያያዝ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የነገር አቀራረብ ሞቅና ደመቅ ያለ ጥምር የአሞጋገት ስልት የነበረው ማራኪ ጥበባዊ ሙግት ነበር። ተሟግቶ ለመርታት፣ ረትቶም እርካታን ለማግኘት፣ ዝናና ክብርን ለመቀዳጀት በቅድሚያ የተሟጋቹን ንቃት፣ ብልህነትና ብርታት ይጠይቅ ነበር።

ከሰውነት እንቅስቃሴው በተጨማሪ የመሟገቻው ቋንቋ በተዋቡ ቃላት፣ በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በተረት፣ በአፈ ታሪክ፣ በእንቆቅልሽና በመሳሰሉት ዘዴዎች የበለጸገ ለዛማ መሆኑ ግድ ይሏል። የእነዚህ ሁሉ ውህድ የችሎቶቹ ነፃ ትርዒት ነበር። በዚህም ምክንያት ወጭ ወራጁና አላፊ አግዳሚው ሁሉ በችሎቱ ይማረክና ይማልል ነበር።" (ስለሺ ለማ፤ ተጠየቅ፤ ገጽ 15)።

አሟጋቾቹም ገዢዎች፣ መኳንንት፣ ባላባቶች፣ ወንበሮች (ዳኞች) ወዘተ. ናቸው። የሙግቱ አካሄድ የራሱ ሥርዓት ነበረው። አቋቋማቸውም ከሳሽ በቀኝ፣ ተከሳሽ በግራ ሲሆን እማኝ መቁጠርና ዋስ መጥራት የመጀመሪያ ተግባር ነበር። ተሟጋቾቹ ኩታቸውን ወይንም ሸማቸውን ወገባቸው ላይ ሸብ አድርገውና ጫፉን በግራና በቀኝ ትከሻቸው ላይ ጣል በማድረግ የተጠየቁ አካሄድ ሳይፋለስ ጉዳያቸውን በጥበባዊ አካሄድ ማሰማት ይጀምራሉ። ሙግታቸውን የሚጀምሩትም "እግዜር ያሳይዎ፣ መልአክ ያመላክትዎ" ብለው በመንደርደር ነበር። ይህ ተማጽኖ ልክ እንደ ዘመናዊ የወንጀለኛና የፍትሐብሔር አንቀጽ በቋሚነት የሚጠቀስ መሆኑን ልብ ይባል።

ለመነሻ ጉዳያችንና ለመድረሻ መደምደሚያችን እንዲረዳን አባትና ልጅ ተሟግተውበት ነበር የተባለ አንድ ጥንታዊ ምሳሌ በማስታወስ እንደምን ለሙግት መንደርደሪያነትና ለመሃላ ጭምር ያገለግል እንደነበር ተመልክተን ለዋናው ጉዳያችን ማነጻጸሪያ እንዲሆን እንዋሰዋለን።

**"በልሃ ልበልሃ!..የአጤ ሥርዓቱን፣**
**የመሠረቱን፣ የአብርሃም እራቱን፣**
**አልናገርም ሀሰቱን፣**
**ሁልጊዜም እውነት እውነቱን።"**

እናም ሙግቱ ይከተላል። ሞጋቹ ልጅ አባቱን "ተጠየቅ?" በማለት ክርክሩን ይጀምራል። ተሞጋቹ አባትም፤ "አልጠየቅም" ብሎ ይንደረደርና መከራከሪያ ሃሳቡን እንዲህ በማለት እንደ ወጨፎ ያዘንበዋል። "ሰማይ አይታረስ፣ ውሃም አይታፈስ፣ መሬት አይተኮስ፣ ብረትም በውሃ አይርስ፣ አባትም አይከሰስ…"

ሞጋች ልጅ መቃወሚያውን እንዲህ ሲል ያቀርባል፤ "ሰማይ በመብረቅ ይታረሳል። ውሃም በእንስራ ይታፈሳል። መሬትም በማረሻ ይተኮሳል። አባትም በጥፋቱ ይከሰሳል።" ተሞጋቹ አባት የክሱን አካሄድ ልብ ብሎ በማጤን ማፋረሻውን እንደሚከተለው ያቀርባል። "ሰማይ ያለ ዓመት ነጎድጓድ አያወርድ፣ ፈጣሪ ያለ በደል ገሃንም አያወርድ፣ ያለ እርሻ በመሬት ላይ እሳት አይነድ፣ ሴትም ያለ እንስራ ወንዝ አትወርድ፣ አባትም ያለ ጥፋቱ ልጁን አይከድ…ስለዚህ አትሞግተኝም ዳግመኛ።" በዚህን መሰሉ ክርክር "ሰማይ አይታረስ፣ አባት አይከሰስ" በሚለው የሙግት ማሳረጊያ በአባት ረቺነት ክርክሩ ተቋጨ ይባላል።

### የኑሯችን "በልሃ ልበልሃ!"

እንደ ጥንቱ የሙግት አካሄድ ሥርዓት የዛሬይቱን ጀንበር እየሞቀች ባለችው ኢትዮጵያ "በልሃ ልበልሃ" እየተባባልን በደጅና በቤት፣ በሜዳና በመንገድ፣ በሚዲያና በሹክሹክታ የምንሟገትባቸውና የምንሞገትባቸው ጉዳዮቻችንና አገራዊ አጀንዳዎቻችን ብዙዎች ናቸው። ማን በሰጣችሁ ሥልጣንና ስለምን መሟገትን መረጣችሁ ተብለን በተቆጭዎቻችን እንዳንጠየቅ ድፍረት የሚሆነን ቀደም ሲል ያስታወስነው የነባሩ ትውፊታችን ውርስና ቀጥለን የምንጠቅሰው የኢዮብ እና የፈጣሪ የሙግት ታሪክ ነው።

ፈጣሪን ተሸቀዳድሞ የከሰሰው ኢዮብ የመከራዎቹና የእንቆቅልሾቹ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ከፈጣሪው ጋር ለተሟገተበት ጥያቄ ከፈጣሪ ከራሱ የተሰጠው መልስ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ይነበባል፤ "ኢዮብ ሆይ! እንግዲህ እንደ ሰው ወገብህን ታጠቅ፤ እጠይቅሃለሁ አንተም መልስልኝ" (ኢዮብ 38፡3)። ለክርክራችን መደላድል የመረጥነው እነዚህን ሁለት የማሳያ ታሪኮች ነው።

ፖለቲከኞች በየመድረኮቻቸው፣ ፍትሕ የተጠሙ ዜጎች በየፍርድ ቤቱ፣ አቅሉን ስቶ ጨርቁን በመጣል ያበደው ኢኮኖሚ የዕለት እንጀራቸውን የቀማቸው ዜጎች በየመገበያያው ስፍራ፣ ተማሪው በየትምህርት ቤቱ፣ ወላጆች በየቤታቸው፣ ሕዝብ በመንግሥት ላይ፣ መንግሥትም በሕዝብ ላይ፣ ምእመናን በየሃይማኖቶቻቸው መሪዎች ላይ፣ ንፁሐን ዜጎች በደም ጥማተኞች ላይ፣ ተጠርጣሪ የፍርድ ተማጻኞች በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ወዘተ. ያልተከፈተ አገራዊ የመካሰሻ ዶሴ፣ የማይደመጥ የብሶት ድምጽ፣ የማይፈስ እምባ እንዲያው በጥቅሉ "በልሃ ልበልሃ" እየተባባልን በመጯጯህም ሆነ በለሆሳስ በነጋ በጠባ የምንሟገትባቸው የአበሳዎቻችንና የተግዳሮቶቻችን ብዛት እንደ ሰማይ ከዋክብት የማይቆጠሩ፣ እንደ ባህር አሸዋ የማይሰፈሩ ለመሆናቸው መስካሪ አያሻውም።

ብዙ ዜጎች "ሰማይ አይታረስ!?" በማለት ተስፋ ቆርጠው የቆዘሙባቸው አገራዊ ጉዳዮቻችንም ተቆጥረው የሚዘለቁ አይደሉም። "ሰማይ እንዴት እንደሚታረስ" የጨለመባቸውና ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ባልገባቸው ግፈኞች ደማቸው ደመ ከልብ የሆነ፣ በእብሪተኞች ሴራና በደል በኑሯቸው ላይ መከራ እንደ ወስከንባይ የተደፋባቸው ዜጎች ብዙ ናቸው ከማለት ይልቅ ቤቱ ይቁጠራቸው ማለቱ ይቀላል። ሰማዩ የሚታረስበት መብረቅ እያስደነገጣቸውም ከቋጥኝ ጋር እንደ መላተም በመቁጠር ለአገር የሚተርፉ በርካታ ምሁራንና ቅን ዜጎች አጉራህ ጠናኝ በማለት "በየጎሬያቸው" መሽገው አህህ እያሉ መቆዘማቸው ሌላው የተቃርኖ እውነታችን ነው።

እውነት እውነቱን እንመስክር ከተባለ የሕዝባችን የበልሃ ልበልሃ የመሟገቻ አካሄድ ቅጥ አምባሩ የጠፋ እስኪመስል ድረስ አገርና ዜጎች በአንድነት ግራ ተጋብተናል፣ ተደነጋግረናል ማለቱ ይቀላል። ለምሳሌ፤ "ብሔራችን ከሰውነታችን" ገዝፎብን አናንቆናል። መታወቂያችን ዜግነታችን ሳይሆን የየት መጣችን የዘር ትምክህት ሆኖብን "ማን ማንን ቢወልድ" ወደሚል የጎጠኝነት አዘቅጥ ውስጥ ከተዘፈቅን ሰነባብተናል።

አገርን ለማገልገል ወንበር የሚያዘው በአወቁና በበቁ መስፈርት ሳይሆን በተዋወቁና በተዛመዱ መሳሳብ ከሆነም ውሎ አድሯል። በአእምሮው ውስጥ ምን እውቀት አለ ሳይሆን "ከበስተጀርባው ማን ደጀን አለው?" የጊዜያችን ፋሽን ሆኗል። የፖለቲካ አሸናፊነት "የጠቅልሎ መግዛት" ላይሰንስ ከሆነም ዓመታት ተቆጥረዋል። ስለዚህም የአገራችን አየር የታጠነው በዜጎች "የበልሃ ልበልህ" ሙግት ነው ቢባል ከእውነት አያርቀንም። ሰማያችንም እንዳይታረስ ጭንጫ የሆነው በዚህን መሰል አገራዊ የልክፍት ደዌ ስለተጠቃን ይመስላል።

### "ኑ እንዋቀስ!?"

ልክ እንደ ዛሬው እንደ እኛ ዘመን መንግሥትና ሕዝብ፣ ሕዝብና ሕዝብ፣ የሃይማኖት መሪዎችና ምእመናኖቻቸው፣ አገልጋዮችና ተገልጋዮች፣ ፖለቲካውና ፖለቲከኞች ግራ እንደተጋቡበት ያለ ሁኔታ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥም መሰል ታሪክ ተመዝግቦ እናነባለን። በዚህ ወቅት ግራ ከተጋበው ሕዝብ ጋር ለመወቃቀስና ለመሟገት ቀድሞ ዝግጁነቱን ያረጋገጠው ልክ ከኢዮብ ጋር እንዳደረገው ፈጣሪ ራሱ ነበር።

እንዲህ በማለት፡- "ኑ እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጣል። እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ይነጣል። እሺ ብትሉ ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ። እምቢ ብላችሁ ብታምጹ ግን ሰይፍ ይበላችኋል። እግዚአብሔር ይህንን ተናግሯል።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 1፡18 - 20)።

መቼም ፈጣሪ በሰው ደረጃ ልክ ራሱን ዝቅ አድርጎ"ኑ እንዋቀስ" ብሎ "ከወደረኞቹ" ጋር ፈቃደኛነቱን ከገለጸ ዕድሜው የተመጠነው ሟቹ የሰው ልጅማ እንዴት ራሱን አዋርዶ ማጎንበስ ይሳነዋል? እርግጥ ነው መንግሥታችን ሊተገብረው በዝግጅት ላይ ያለው ሁሉን አካታች የብሔራዊ ምክክር መድረክ "ለመነጋገሩና ለመወቃቀሱ" ጥሩ ጅማሮ እንደሆነና ሊበረታታ እንደሚገባ እናምናለን።

ብሶተኞቹ፣ እብሪተኞቹና በደም ውርርድና በባሩድ ጭስ ካልታጠን እያሉ የሚፎገሉት የዚህች አገር ልበ ደንዳ የጫካ ጦረኞችም ለጥሪው በጎ ምላሽ ሰጥተው ወደ ሰላማዊ "የመዋቀሻና የመነጋገሪያ" መድረክ እንደሚመጡ ተስፋ ይደረጋል። ያለበዘለዚያ ግን በግፉ በለው የትእቢት ቀረርቶና በይዋጣልን የጅል ፉከራ አሸንፎ የተጨበጨበለት፣ ድል ቀንቶትም የተመሰገነ ስለሌለ የሚመለከታቸው ሁሉ ልብ ተቀልብ ሆነው ቢያስቡበት ይበጃቸዋል።

አገሬ እንደ ሰማይ የራቁና እንደ ደመና የከበዱ በርካታ መከራዎችን እየተሻገረች ስለመጣች በየወቅቱ ለሚገጥሟት ተግዳሮቶች ሁሉ እንዴት ማለፍ እንደምትችል ዘዴውንም ሆነ ጸሎቱን ታውቅበታለች። በአድዋ የፍልሚያ ሜዳ አያቶቻችን የተጎናጸፉት የድል ታሪክ "ሰማይን ከማረስ" በምን ይተናነሳል። አዎን "የጥንቱ አድዋ ሰማይ በነፃነት ፍቅር መብረቅ ታርሷል፣ ተከታታይ የጦርነቶች የባሩድ ጭስም በጀግኖች አባቶቻችን ደምና ላብ ተዳፍኗል።

ከአባይ ወንዛችን ውሃም የብርሃን ጸዳል ፈልቋል። ጦም ማደር የለመደው መሬታችንም በኩታ ገጠም እርሻ ስንዴ ተመርቶበት ከራሳችን ተርፎ ሌሎችንም ሊመግብ ጫፍ ላይ መድረሱ እየተነገረን ነው። ማንም ይሁን ማን ሕዝብን በክፋቱ የሚለክፍ ከሆነ የቀን ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በጥፋቱ ይከሰሳል፤ እጁም በሰንሰለት ካቴና ይጠፈራል።

የሚበጀውና የሚያዋጣው "በልሃ ልበልሃ" እየተባባልን በየአደባባዩ፣ በየጓዳችን፣ በየሚዲያዎቻችንና በየመሸሸጊያ ዋሻችን ውስጥ በማድፈጥ የምንካሰስባቸው መከራዎቻችን መፍትሔ በሚያገኙበት ጉዳዮች ላይ መመካከሩ ብቻ ነው። "ሰማይ እንደማይታረስ ሁሉ የሚመጣውን እናያለን!" እየተባለ በመንግሥት ሹመኞችም ዘንድ ሆነ በአንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚፎከረው ቀረርቶ "የታሪካችንን ጠባሶች" በማስታወስ ቢለዝብ ለሁላችንም ይበጃል።

"ሰማይ በመብረቅ መታረሱን" ትናንት በሚገባ አስተምሮናል። ይህ መብረቅ የሚወክለው በተፈጥሮ ዳመና ውስጥ የሚከሰተውን ኤሌክትሪካዊ ብርቅርቅታ ብቻ ሳይሆን የግፉዓን ሕዝብን የተባበረ ድምጽ ጭምር ነው። ድምጹ እንኳን የምድሩን ግፍ ቀርቶ ጸባኦትን የማናወጥና የመነቅነቅ አቅሙና ብርታቱ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ቀኑ ሳይዳምን ዛሬውኑ በምናለቅስባቸውና በተራብንበት ዘርፈ ብዙ አገራዊ ጉዳዮቻችን ዙሪያ በሆደ ሰፊነት መወያየት ልንጀምር ግድ ይላል። መብረቁ ቀድሞ አንጎዳጉዶ ዶፉን መልቀቅ ከጀመረ ማጣፊያው የሚያጥረው እከሌ ከእከሌ ሳይባል ለሁሉም ዜጋ ነው። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የወጪ ንግዱ እምርታ

ፍሬሕይወት አወቀ

«የኢትዮጵያ ባለ ልዩ ጣዕም ምርትን ይግዙ» በሚል መሪ ቃል ባለፈው ሳምንት የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ቀን በፓናል ውይይት እና በአውደ ርዕይ ተከብሯል። በወቅቱም በተመረጡ ላኪዎች ከግብርና፣ ከኢንዱስትሪና ከማእድን የተመረጡ 12 አይነት የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ምርቶች ለእይታ ቀርበዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ ያካሄደው ይህ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ቀን መድረክ የኢትዮጵያን ምርቶች መለያ ለማድረግ፣ የገበያ ፍላጎቶችንና መዳረሻዎችን ለማስፋትና አዳዲስ ምርቶችን ወደ ወጪ ንግድ ገበያው ለማስገባት፣ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ እንደሚጠቅም ተጠቁሟል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በውጭ ምንዛሬ እጥረት በብዙ እየተፈተነች ያለችው ኢትዮጵያ ካለፉት ዓመታት በተሻለ በተጠናቀቀው 2014 በጀት ዓመት በወጪ ንግድ አፈጻጸም አመርቂ ውጤት አስመዝግባለች። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በወጪ ንግድ አበረታች ውጤት ካስመዘገበችባቸው ዘርፎች መካከል ደግሞ የአንበሳውን ድርሻ የወሰደው የግብርናው ዘርፍ እንደሆነም ተጠቁሟል። ከግብርናው ዘርፍ ደግሞ ቡና በታሪክ ታይቶ በማያውቅ መልኩ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ አስገኝቷል። ግብርና ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ 20 በመቶውን መሸፈኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ።

እውቅና ከተሰጣቸው ላኪዎች መካከል በሆርቲካልቸር ዘርፍ የተሰማራውና በእስራኤላውያን ባለሃብቶች የሚመራው ጀይ ቴክ የተሰኘው ድርጅት አንዱ ነው። የድርጅቱ የእርሻ ሥራ አስኪያጅ አቶ ብሥራት ኃይለስላሴ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ በቢሾፍቱና ለገዳዲ አካባቢዎች አንድ መቶ ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ላይ በሆርቲካልቸር የሥራ ዘርፍ ተሰማርቷል። ላለፉት 20 ዓመታትም የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንዲሁም የእጸጣዕም ምርቶችን እያመረተ ለውጭ ገበያ እያቀረበ የሚገኝ ሲሆን፣ በዋናነት ለአውሮፓ ገበያ ራሺና ኖርዌ ምርቶቹ በስፋት ይልካል።

ከድርጅቱ ምርቶች መካከል እጸጣዕም በዋናነት ይጠቀሳል፤ እጸጣእም ለምግብ ማጣፈጫነት የምንጠቀምባቸውና አንዳንዶቹም የመድሃኒትነት ባህሪ ያላቸው እንደ ሮዘመሪኖ፣ ናና፣ ጦስኝ፣ ድንብላል፣ ጠጅሳርና የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን፣ ድርጅቱም አጠቃላይ 26 የሚደርሱ የእጸጣዕም ምርቶችን ያመርታል። ከአትክልትና ፍራፍሬ መካከልም የአበባ ጎመን፣ ብሮኮሊ፣ ፍሬንች ቶማቶ፣ ቲማቲም፣ ሰላጣ፣ ኩከንበርና የመሳሰሉትን በማምረት ለውጭ ገበያ በስፋት ያቀርባል።

በተያዘው በጀት ዓመትም ድርጅቱ በመጠን ከፍ ያለ ምርት ወደ ውጭ ገበያው በመላክ ዳጎስ ያለ የውጭ ምንዛሪ ማስገባት መቻሉን አቶ ብስራት ጠቅሰው፣ በዋናነት የወጪ ንግድ ሥራ ሲሰራ በዓመት ውስጥ ምን ያህል ምርት ወደ ውጭ ገበያ መላክ እንዳለበትና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ዕቅድ ተይዞ እንደሚሠራ ይገልጻሉ። በተጠናቀቀው 2014 በጀት ዓመትም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኪሎ ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ አቅዶ፣ እቅዱንም ሙሉ ለሙሉ ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል። በዚህም ድርጅቱ ከ25 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማስገኘት በመቻሉ ተሸላሚ መሆን ችሏል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያዘጋጀው መድረክ በአይነቱ የተለየና እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ አቶ ብስራት በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ገልጸዋል፤ በተለይም በወጪ ንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አካላት ምርቶቻቸውን ለእይታ በማቅረብ ምን አይነት ምርቶች ወደ ውጭ ገበያ እየተላኩ እንደሆነ መረዳት ተችሏል ይላሉ። በተጓዳኝም የተለያዩ ምርቶችን በማየት የልምድ ልውውጥ ማድረግ መቻሉንና አጠቃላይ አገሪቷ በወጪ ንግድ ዘርፉ የት ላይ እንዳለች ግንዛቤን መፍጠር ማስቻሉንም ይናገራሉ።

አገሪቷ የተለያዩ ፈተናዎችን ተቋቁማ በተለይም ለአገሪቷ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት የሚችለው የወጪ ንግድ ሳይቆራረጥ ማስቀጠልና የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉ ትልቅ ነገር ሆኖ እንዳገኙት ጠቅሰው፣ መንግሥትም ለዘርፉ ተዋናዮች ዕውቅና መስጠቱ እጅግ የሚያበረታታና ጥሩ ስሜት መፍጠር



**ሚኒስቴሩ በወጪ ንግድ ከ25 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ላስገኙ ላኪዎች እውቅና ሰጥቷል**

የቻለ መሆንም ተናግረዋል። ይህም በቀጣይ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ከዚህ በበለጠ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ማስገባት እንዲቻል የሚያነሳሳ የሞራል ስንቅ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

በመድረኩ የተገኙት የዘርፉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት እንዲገነዘቡ መደረጉና ችግሮቹንም ለመፍታት ቃል መግባታቸውን አንደ ስኬት የተመለከቱት አቶ ብስራት፣ ችግሮቹም በኃላፊዎቹ የሚፈታ ስለመሆኑ እምነት አድሮባቸዋል። ይህም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚያስችል ይጠቁማሉ፤ መድረኩንም የተሳካ ሲሉ ገልጸውታል።

እንደ አቶ ብስራት ገለጻ፤ ድርጅቱ በግብርናው ዘርፍ የተሰማራ እንደመሆኑ በቀጣይ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ገቢውን በዛው መጠን ከፍ ለማድረግ አቅዷል። የበለጠ ዘመናዊ መንገድን በመከተል ተጨማሪ ምርት ለማምረት መታቀዱንም ያመለክታሉ።

በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ለውጡን ተከትሎ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የንግድ ስርዓቱን ለማዘመን እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሻሻል የሪፎርም ስራ መከናወኑን አስታውቀዋል። የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከዓለም ንግድ ስርዓት ውስጥ ተገቢው ስፍራ እንዲኖረው ለማስቻል በየዘርፉ የሚያስፈልጉ ፖሊሲዎችን ከመቅረፅ ጀምሮ የተለያዩ ንቅናቄዎች መደረጋቸውንም ነው ያመለከቱት። በዚህም ለበርካታ አመታት ሲሰራበት የነበረውን የንግድ ህግ የማሻሻል ስራ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህግ ሆኖ እንዲወጣ መደረጉን አንስተዋል።

አፈ ጉባኤው የኢኮኖሚ ሪፎርሙ የወጪ ንግድ ገቢን በማሳደግ በአለም መድረክ የኢትዮጵያን ተሳትፎ ከማሳደግ በላይ በችግሮች ውስጥ ሆኖም ጠንካራና የማይበገር ኢኮኖሚ መገንባት እንደሚቻል የታየበት ነው ብለዋል። በቀጣይም እምቅ ሀብቶችን በመጠቀም የውጭ ዕዳ እንዲቀንስ እና ኢኮኖሚው እንዲዳብር ውጤታማ አሰራር እንደሚከተል ማስታወቃቸውን የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች አመልክተዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ ኢትዮጵያ በተጠናቀቀው 2014 በጀት ዓመት በወጪ ንግድ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለች ጠቅሰዋል። ለተገኘው ውጤትም የተጀመሩ ሁለንተናዊ የሪፎርም ሥራዎች ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ሚኒስትሩም ጠቁመዋል።

ከሪፎርም ስራዎቹ መካከል ከ60 ዓመት በላይ ያስቆጠረው የአገሪቱን የንግድ ህግ ከማሻሻል ጀምሮ በሥራ ላይ የነበሩ የኢንቨስትመንት ህጎች ላይ ማሻሻያዎች ማድረግ፤ የካፒታል ገበያን ለመጀመር የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማከናወን፣ የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት ሂደቶችን ለማጠናቀቅ የተሰሩ ሥራዎች፤ የአህጉራዊ የንግድ ቀጠና ስምምነቶችን በመፈረም ወደ ተግባር መግባት፣ የንግድ ፖሊሲ የወጪ ንግድ ስትራቴጂ እና የጥራት ፖሊሲዎችን የማዘጋጀት ሥራዎች እንደሚጠቀሱ አብራርተዋል። እነዚህ ስራዎች የአገራዊ ለውጡ ትልቅ አካል ተደርገው የሚወሰዱ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

**በ2014 በጀት ዓመት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ነጥብ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ከወጪ ንግድ ተገኝቷል። አፈጻጸሙም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 13 ነጥብ ስምንት አንድ በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። በዘርፍ ደረጃ ሲታይ ግብርና፣ ኢንዱስትሪና ማዕድን ከፍተኛውን ደረጃ ይዘዋል። ለተመዘገበው ውጤት ሁሉም ዘርፎች ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል**

ለተመዘገበው ከፍተኛ የወጪ ንግድ ገቢ የመንግስት ተቋማት እና የግሉ ዘርፍ የበኩላቸውን ሚና እንደተወጡ ተናግረው፣ በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በትብብር እንሰራለን ብለዋል። እውቅና እና ሽልማት የተሰጣቸው ላኪዎች በበኩላቸው በቀጣይ የበለጠ ለመስራት እንዲሁም በግልፀኝነት እና በታማኝነት ለማከናወን ሽልማቱ የሚያበረታታቸው እንደሚሆንም ነው ሚኒስትሩ የተናገሩት።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በ2014 በጀት ዓመት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ነጥብ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ከወጪ ንግድ ተገኝቷል። አፈጻጸሙም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 13 ነጥብ ስምንት አንድ በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ይህም በዘርፍ ደረጃ ሲታይ ግብርና፣ ኢንዱስትሪና ማዕድን ከፍተኛውን ደረጃ ይዘዋል፣ ለተመዘገበው ውጤት ሁሉም ዘርፎች ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል።

የወጪ ምርቶች በመጠንም ሆነ በጥራት ጨምረዋል። ለአብነትም ቡና በከፍተኛ ደረጃ በመጠን የጨመረ ሲሆን፤ የቁም እንስሳት፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችም እንዲሁ በከፍተኛ መጠን ለውጭ ገበያ ተልከዋል። ከፍተኛ መጠን ያላቸው የተለያዩ ምርቶች በኮንትሮባንድ እየወጡም፣ የወጪ ምርቶቹ መጨመር መቻላቸው አገሪቷ በወጪ ንግዱ ከፍተኛ አቅም እንዳላት ያመለክታል። አገሪቷ በጦርነት፣ በጸጥታ ችግርና በተለያዩ ችግሮች ውስጥም ሆና በአሁኑ ወቅት የወጪ ምርቶች መጠን መጨመር መቻሉ አበረታች ሊባል ይገባዋል።

ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸውን የወጪ ንግድ ምርቶች ለዓለም ገበያ ይበልጥ በማስተዋወቅ የገበያ ፍላጎቶችንና መዳረሻዎችን በማስፋት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የማሳደግ ዕቅድ መያዙንም ነው አቶ ገብረመስቀል ያስታወቁት። ለዚህም በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ ገቢ ማስመዝገብ የቻሉ የወጪ ንግድ ላኪዎች በመድረኩ ምርቶቻቸውን እንዲያሳዩ መደረጉን፣ በወቅቱ ለናሙና የቀረቡት ምርቶችም የዓለም ገበያን ሰብረው በመግባት ከሌሎች አገራት ጋር ተወዳዳሪ መሆንና ከፍተኛ መጠን ያለውን የውጭ ምንዛሪ ወደ አገሪቷ ማስገባት የቻሉ ናቸው ብለዋል።

በአገሪቱ ከሚገኙና በሺዎች ከሚቆጠሩ የወጪ ንግድ ላኪዎች መካከል ከ25 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ለአገራቸው ማስገባት የቻሉት ላኪዎች «አርበኞች» ስለመሆናቸው የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ ላኪዎቹ ኢትዮጵያ በበጀት ዓመቱ ከፍተኛ መጠን ያለውን የወጪ ምርቶች ለወጪ ንግድ እንድትልክና የተሻለ ውጤት እንድታስመዘግብ በማድረግ ከፍተኛ ድርሻን መወጣት ችለዋል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ከፍተኛውን ገቢ በማስገኘት ረገድ የግብርናው ዘርፍ ቀዳሚ በመሆን የምጣኔ ሀብቱ ዋነኛ የገቢ መሰረት እንደሆነም ቀጥሏል። በአጠቃላይ ለወጪ ገቢ ንግዱ የግብርናው ዘርፍ 72 በመቶ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ 12 በመቶ እንዲሁም የማዕድን ዘርፉ 14 በመቶ አስተዋጽኦ ማበርከት ችሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ስድስተኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንደኛ አመት የሥራ ዘመን 16ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ኢትዮጵያ በወጪ ንግድ ዘርፍ ያስመዘገበች እምርታ በጣም በጣም ግዙፍ ነው ብለውታል። ይህንን ውጤት አስጠብቆ ለጥቂት ዓመታት መጓዝ ከተቻለ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የንግድ መዛባትና የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል ሲሉ አስታውቀዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በ2002 በጀት አመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር ኤክስፖርት አድርጋ እንደነበር፤ ጉድስ (goods/ ሸቀጦች) ከ2002 እስከ 2012 ዓ.ም ሶስት ቢሊዮን ለመድረስ ትንገዳገድ ነበር። በ10 ዓመት ውስጥ አንድ ቢሊዮን ገደማ መጨመር ተችሏል። ባለፈው በጀት አመትና በዘንድሮው በጀት ዓመት በተከናወነው የሪፎርም ሥራ በሁለት ዓመት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ በመጨመር ዛሬ በጉድስ እና ሰርቪስ/በሸቀጦችና አገልግሎት/ ኤክስፖርት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ መገኘት ተችሏል።

በጉድስና በሰርቪስ ባለፈው ዓመት ከነበረው ዘንድሮ ጭማሪ አሳይቶ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኤክስፖርት ውጤት ተገኝቷል። ሰርቪስ ደግሞ በ25 በመቶ አድጎ ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ አግኝተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሰርቪስና በኤክስፖርት አስር ቢሊዮን ሲገባ ደግሞ በሁለቱ ከ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር አካባቢ የሚገመት ተጨማሪ ሃብት ማፍራት መቻሉን ተናግረዋል። የሰርቪስ ከፍ ይላል፤ በዚህ ደግሞ በሁለቱ ዓመት ውስጥ አንድ እንጨምርበታለን። ይሄ በጣም ትልቅ እምርታ ነው። ግን ሊያዘናጋን አይገባም፤ ከምንፈልገው አሁንም ሩቅ ስለሆንን ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል ማለታቸው ይታወሳል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ የወጪ ንግድ ገቢን ወደ አምስት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ ታቅዶ እየሰራ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## እያዝናኑ ማስተማር እንዲህ ነው!

**ዋለልኝ አየለ**

የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች የሚመሩትን ፕሮግራም ‹‹እየተዝናናችሁ የምትማሩበት›› ሲሉ እንሰማለን። እንደዚህ ብለው ግን የሚነግሩን ስለአንዲት የውጭ አገር ዝነኛ አርቲስት የእርግዝና ድግስ (ቤቢ ሻወር) ሊሆን ይችላል። በበኩሌ አያዝናናኝም አያስተምረኝም!

የዛሬ ትዝብቴ ግን ወቀሳ ሳይሆን አድናቆት ነው። በነገራችን ላይ ‹‹ትዝብት›› ሲባል ብዙዎቻችን ትዝ የሚለን ወቀሳ ብቻ ነው። አድናቆትም ትዝብት ነው። ለምሳሌ፤ እንደ ምርጫ ባሉ ትልልቅ ጉዳዮች ላይ ታዛቢ ተብለው የሚቀመጡ አሉ። ስህተትን ብቻ ለመታዘብ ሳይሆን ያስተዋሉትን ጥሩ ነገርም ለመመስከር ነው።

በትዝብት ስም ከሚጻፉ ጽሑፎች (የእኛን ጨምሮ) የምናነበው መስተካከል አለባቸው የምንላቸውን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ነው፤ ወቀሳዎች ይበዛሉ። ትክክል ነው! መስተካከል ያለባቸው ነገሮች እንዲስተካከሉ መታዘብና መውቀስ ያስፈልጋል። በዚያው ልክ ግን ጥሩ የሆኑ ነገሮችንም ማድነቅ ሌሎች ጥሩዎችን መፍጠር ነው።

ወቅቱ የክረምት ወቅት ነው። ለተማሪዎች የእረፍት ወቅት ስለሆነ በየቤታቸው ናቸው። የእረፍት ወቅት ነው ማለት ግን ከትምህርት ይርቃሉ ማለት አይደለም። መስከረም ላይ ወደሚቀጥለው ክፍል ስለሚገቡ የሚቀጥለውን ክፍል የትምህርት አይነቶች ከወዲሁ ይጀምራሉ። ያለፉትን ክፍልም ለሚቀጥለው ስለሚያግዝ ይከልሳሉ።

እነዚህን ሁሉ ነገሮች ያስታወሰኝ ባለፈው እሁድ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የመዝናኛ ጣቢያ (ኢቲቪ መዝናኛ) ላይ ያየሁት ነገር ነው። ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ትምህርታዊ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች ናቸው። ሙሉ የፕሮግራሙን ይዘት ለመግለጽ ደጋግሞ ማየት ቢጠይቅም ባየሁበት ዕለት፤ ጥያቄዎችን የሚያብራራ መምህር ከስቱዲዮ ከጋዜጠኛዋ ጋር ይቀመጣል። አየር ላይ ጥያቄ ይጠየቃል፤ ተማሪዎች በስልክ እየገቡ ይመልሳሉ።

ጥያቄዎቹ እንደሌሎቹ ጥያቄና መልስ ውድድሮች የጠቅላላ ዕውቀት ሳይሆኑ መደበኛ የትምህርት ጥያቄዎች ናቸው። ተማሪዎች በስልክ ይመልሳሉ፤ ከመለሱ በኋላ ስቱዲዮ ያለው መምህር ያብራራል። ልክ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚጠየቁት አይነት ማለት ነው። የቴሌቪዥኑ ስክሪን ላይ Which one of the Following.... የሚለውን ስመለከት ወደ ልጅነቴ ነው የተመለስኩት።

መጀመሪያ እንዳየሁት፤ እንዴት ይሄን ትምህርት የመዝናኛ ጣቢያ ላይ ያደርጉታል ብየ ነበር። እያደር ሳስበው ግን ተማሪዎች የእረፍት ጊዜ ላይ ስለሆኑ እየተዝናኑ የሚማሩት ነው። በዚያ ላይ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በሚተነተኑበት የዜና ጣቢያ ቢሆን ልጆች አያዩትም። እየተዝናኑ መማር ማለት ይህ ነው።

መምህራን አንዳንድ ጊዜ ‹‹እየተጨናነቃችሁ አታጥኑ›› ይላሉ። አሁን ወቅቱ ክረምት ነው፤ ተማሪዎች በፈተና የሚጨናነቁበት ጊዜ አይደለም። እስከ አሁን የተማሯቸውንና በሚቀጥለው ክፍል የሚማሯቸውን በዚህ ሁኔታ ማጥናታቸው ወደ ውስጣቸው እንዲሰርፅ ያደርጋል። በዚያ ላይ ደግሞ ጥያቄ ለመለሱ ተማሪዎች የመጽሐፍ ስጦታ ይሰጣቸዋል። ይህም ሌሎች ተማሪዎች እንዲነቃቁና እንዲከታተሉ ያደርጋል። እያዝናኑ ማስተማር እንዲህ ነው!

በዚሁ እግረ መንገድ በሌሎች የቴሌቪዥን ጣቢያዎችም አይቼ ካመሰገንኳቸው ልጠቃቅስ። ይሄም እያዝናና የሚያስተምር ሆኖ ያገኘሁት ነው። አዲስ ሚዲያ ኔቶርክ (አዲስ ቲቪ) ላይ ጋምቤላ ሆቴል ውስጥ የተዘጋጀ አንድ የመዝናኛ ፕሮግራም አየሁ። ተወዳዳሪዎቹ የሚጠየቁት በክረምት ወቅት አርሶ አደሩ የሚያንጎራጉራቸውን የስነ ቃል ግጥሞች ነው። ለከተሜ ነዋሪ ከባድ ይመስላል። ባለማወቃቸውም ስንኙን ራሳቸው በሚፈልጉት መንገድ (ቤት እንዲመታ ብቻ) ጨረሱት፤ ይሄ ያዝናናል፤ የአርሶ አደሩን ጥበብና ቅኔ ማስታወሱ ደግሞ ትምህርት ነው። መጨረሻ ላይ ጋዜጠኛዋ ጥያቄዎቹን በሚገባ ታብራራለች።

በቴሌቪዥንየመዝናኛፕሮግራሞችብዙምአስተውየው የማላውቀውን ከዚሁ ከአዲስ ቲቪ ያስተዋልኩት አርሶ አደሩ ለሚያመርታቸው የቅመማቅመምና እህል አይነቶች ትኩረት መስጠቱ ነው። ተወዳዳሪዎቹ የእነዚያን የቅመማቅመም አይነቶች እንዲናገሩ መደረጉም ሌላው የተወዳዳሩበት ነበር። ቀላል ይመስለን ይሆናል፤ ዳሩ ግን ልብ ያልተባለና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የአገር ምርት ነው።

አዲስ ሚዲያ ኔቶርክ የአዲስ አበባ ነው። አብዛኛው ተከታታዩ የከተማ ነዋሪ ነው። በመዝናኛ ፕሮግራም ይህን ያደረገውም ለዚህ ነው። ለገጠሩ ማህበረሰብ ቢቀርብ ምንም አያዝናናም ነበር። አንድን ገበሬ ‹‹ጤና አዳም ምንድነው?›› ብንለው ስቁብን ነው የሚያልፍ። የከተማ ነዋሪዎች ሲፈተኑበት ግን ያዝናናል። እያዝናኑ ማስተማር እንዲህ ነው።

ሌላው እያዝናኑ ማስተማር ያስተዋልኩት ደግሞ በኢትዮጵያ ብሮድካስት ሰርቪስ (ebs) ቴሌቪዥን ነው። በነገራችን ላይ ብዙ ሰው የኢ. ቢ. ኤስ እና ኢ. ቢ. ሲ. ስም ይምታታበታል።

ኢ. ቢ. ኤስ ‹‹ቅዳሜ ከሰዓት›› የሚባል ፕሮግራም አላቸው። ብዙ እያዝናኑ የሚያስተምሩ ፕሮግራሞች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ በቅርቡ የተጀመረ ‹‹ተከፍሏል›› የምትል አጭር ፕሮግራም አለች። እያዝናናች የምታስተምር ናት።

ካሜራው ተሽከርካሪ ውስጥ በድብቅ ይቀመጣል። ጋዜጠኛዋ የተጎሳቆለች ሴትዮ መስላ፤ ፊቷን ተሸፋፍና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች የያዙ (ለምሳሌ ጉሊት) አጠገብ ትሄዳለች። የያዙትን ነገር ትጠይቃለች። ዋጋውን ይነግሯታል። ብዙ የምትገዛ መስላ ታስቆጥራቸዋለች። መጨረሻ ላይ በዕለቱ ሊያገኙ የሚችሉትን ገቢ ትጠይቃቸውና የዕለቱን ገቢያቸውን ኢ. ቢ. ኤስ ቴሌቪዥን እንደሚሸፍን ትነግራቸዋለች። የተሸፋፈነችውን ተገልጣ፣ ራሷን አስተዋውቃ ድብቅ ካሜራ መኖሩን አሳይታ ከዝናብ ወይም ከፀሐይ ላይ ተነስተው ወደቤታቸው እንዲሄዱ ታደርጋቸዋለች። በዚያን ዕለት ገቢያቸውን ከቴሌቪዥን ጣቢያው አግኝተው ከፀሐይ ወይም ዝናብ እረፍት አደረጉ ማለት ነው።

በቆይታዋ ውስጥ ከሰዎቹ ጋር የምታደርጋቸው ጭውውቶች አስቂኝ ናቸው። በተለይም መጨረሻ ላይ የያዙትን ዕቃ ዋጋ ወይም በዕለቱ የሚያገኙትን ገቢ እንደሚከፈልላቸው እና እየተቀረጸ መሆኑን ሲያውቁ የሚያሳዩት ድንገተኛ ግርምት ያስቃል። እናቶችና አባቶች ከሆኑ ደግሞ አብዝተው ይመርቃሉ። እያዝናኑ ማስተማር ማለት እንዲህ ነው።

በብዙ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ላይ የሚነሳው ቅሬታ የውጭ መገናኛ ብዙኃን አሰራሮችን መኮረጅ ነው። ከራስ ፈጠራ ይልቅ የውጭ አገራትን አይቶ ለማስመሰል መሞከር ነው። የራሳችን የሆነ ነገር የሚያዝናና አይመስለንም። ግን ደግሞ ለባህላችን ትኩረት አልሰጠንም እያልን እንታዘባለን፣ እንወቅሳለን።

ከእነዚህ ሦስት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ያስተዋልኳቸው ነገሮች እያዝናኑ ያስተማሩኝ ናቸው። ምንም እንኳን የተማሪዎች ጥያቄ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች ላይ ቢሆንም፤ ልጆችን በዚህ መንገድ መቅረጽ የእኛ የአዋቂዎች ድርሻ ነው። ልናበረታታው የሚገባን እኛ ነን። ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለመምህራንም የሚሆን ነው፤ በየዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎችም የሚሆን ነው። የኬሚስትሪ ወይም ፊዚክስ ጥያቄ ሲጠየቅ ፋብሪካ ውስጥ የሚሰራ ሰው ይማርበታል፤ ጂኦግራፊም ወይም ሌላ የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ሲጠየቅም እንደዚሁ በየዘርፉ ያለ ሰው እየተዝናና ይማርበታል።

የአርሶ አደሩን የስነ ቃል ጥበብ ውጤቶች ማስታወስ ለከተሜው እንደ አዲስ ያዝናናዋል፤ ለሚያውቀውም ያስታውሰዋል፤ ታሪክና ባህሉም እንዲሰነድ ያደርጋል።

በማህበራዊ ገጾች (ዩ ትዩብ) ‹‹ሰርፕራይዝ፣ ፕራንክ...›› እየተባለ የሚያዝናኑ ነገሮችን እናያለን። በዋናዎቹ መገናኛ ብዙኃን ደግሞ እንደነ ኢ. ቢ. ኤስ እያዝናኑ የሚያስተምርና የበጎ አድራጎት ሥራ የሚሰራ ፕሮግራም ሊመሰገን ይገባል። ያ ዕድል ያጋጠማቸው ሰዎች ቀኑን ሙሉ ጉሊት ቢውሉ ምናልባትም ምንም ሳይሸጡ ሊውሉ ይችላሉ። ቴሌቪዥን ጣቢያው ግን በዕለቱ ሊያገኙ የሚችሉትን ይከፍላቸዋል፤ በድርጊቱም ዘና ብለው ወደቤታቸው ይሄዳሉ። እያዝናናችሁ የምታስተምሩ መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኞች ምሥጋና ይገባችኋል!

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ እና ዩክሬን እያደረጉት ባለው ግጭት ዘመን አፈራሽ ድሮኖች ጥቅም ላይ ውለዋል

በሩሲያ ዩክሬን ጦርነት በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰው አልባ አውሮፕላኖች [ድሮኖች] የዩክሬን ሰማይ ላይ ይከንፋሉ። እነዚህ ድሮኖች የተለያየ ተልዕኮ አላቸው። አንዳንዶቹ የጠላትን መገኛ እና ይዞታዎችን ይለያሉ። ወታደራዊ ግብዓቶችን ከሚያጓጉዙት በተጨማሪ በጠላት ኃይል ላይ ሚሳኤል ለመተኮስ ጥቅም ላይ የሚውሉም አሉ። በዚህ ጦርነት ተሳታፊ የሆኑት ሁለቱም ወገኖች፤ ለወታደራዊ ዓላማ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን እየተጠቀሙ ነው።


የዩክሬን ጦር በዋነኛነት የታጠቀው ቱርክ ሠራሹን ባይራክታር ቲቢ 2 ድሮኖች ነው።

ባይራክታር ቲቢ 2 ለስለላ ወይም የጥቃት ተልዕኮዎችን እንዲወጣ ተደርጎ የተሰራ ነው። በመጠን አነስተኛ አውሮፕላን ያክላሉ። ካሜራ የተገጠመላቸው ሲሆን በጨረር የሚዘወሩ ቦምቦችን መጣል ይችላሉ።

የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ሲጀመር ዩክሬን “ከ50 ያነሱ” ባይራክታር ቲቢ 2 ድሮኖች እንደነበሯት የሚናገሩት የሮያል ዩናይትድ ሰርቪስ ተቋም (ሩሲ) ባልደረባ የሆኑት ዶ/ር ጃክ ዋትሊንግ ናቸው። ሩሲያ በበኩሏ በመጠን አነስተኛ እና በሚሰጡት አገልግሎትም መሠረታዊ የሚባሉትን ኦርላን-10 ድሮኖችን ትጠቀማለች ይላሉ።

“ሩሲያ በሺዎች በሚቆጠሩ ድሮኖች ነው ጦርነቱን የጀመረችው። “እነዚህ ሩሲያ የምትጠቀማቸው ድሮኖች ካሜራ የተገጠመላቸው ናቸው። ሚሳኤል መተኮስም ይችላሉ። የሁለቱም ወገኖች ድሮኖች የጠላትን መገኛ በመለየት እና ዒላማዎች የተጠበቁ እንዲሆኑ በማድረግ ስኬታማ ናቸው።

“ኦርላን-10 ድሮኖች የጠላትን መገኛ በለዩ ከሦስት እስከ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ የሩሲያ ጦር መሣሪያ በጠላት ላይ ጥቃትን ይፈጽማል” ይላሉ ዶ/ር ዋልቲንግ። ያለ ድሮኖቹ እገዛ ጥቃት ለማድረስ ከ20 እስከ 30 ደቂቃ ሊጠይቅ ይችላል። ዶ/ር ማርቲና ሚሮን ለንደን በሚገኘው ኪንግስ ኮሌጅ የመከላከያ ተመራማሪ ናቸው። ዩክሬን ያላትን ጦር መሳሪያ በደንብ እንድትጠቀም ድሮኖች ትልቅ ሚና አላቸው ይላሉ።



“በቀደመው ጊዜ የጠላትን ዒላማ ለመለየት ልዩ ኃይል መላክ ያስፈልግ ነበር። ይህ ልዩ ኃይል ሥራውን አከናውኖ ሲመለስ የተወሰኑትን ሊሰዋ ይችላል። አሁን ካጡም የሚያጡት ድሮን እንጂ የሰው ሕይወት አይደለም።”በጦርነቱ የመጀመሪያ ሳምንታት ዩክሬን ያሰማራቻቸው ባይራክታር ቲቢ 2 ድሮን ሰፊ ሙገሳን አግኝተው ነበር።“የጠላትን የመሣሪያ ማከማቻ ሲያወድሙ ታይተዋል። ሞስክቫ የተባለችው መርከብ እንድትሰጥምም ሚና ነበራቸው” ይላሉ ዶ/ር ሚሮን።

ሆኖም አብዛኞዎቹ ባይራክታር ቲቢ 2 ድሮኖች በሩሲያ የአየር መቃወሚያ ሥርዓት ከጥቅም ውጪ ሆነዋል። “በመጠን ትልቅ መሆናቸው፣ በከፍተኛ ፍጥነት አለመብረራቸው፣ የሚመሩበት ከፍታ አነስተኛ መሆኑ ለመመታት ቀላል አድርጓቸዋል” ይላሉ ዶ/ር ዋልቲንግ።

የጦር ድሮኖችን ለመተካት ውድ ናቸው። የአንዱ ባይራክታር ቲቢ 2 ድሮን ዋጋ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ገደማ ነው። ሁለቱም ወገኖች ወደ መደበኛዎቹ ድሮኖች ፊታቸውን እያዞሩ ነው። በተለይም ዩክሬን ይህን መንገድ መከተል ጀምራለች። 1700 ፓውንድ የሚያወጣው ዲጂአይ ማቪክ 3 ደግሞ ተጠቃሽ ድሮን ነው። አንድ የዩክሬን የድሮን አምራች የአገሪቱ ጦር ከ6000 በላይ ድሮኖች እንዳሏት ግምቱን አስቀምጧል። ይህን ማረጋገጥ ግን አልተቻለም።

ለሌሎች አገልግሎቶች የተሰሩና በቀላሉ በገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉ መደበኛ ድሮኖች ላይ ቦንቦችን መግጠም ይቻላል። ይሁን እንጂ እነዚህ ድሮኖች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት የጠላትን መገኛ ለመለየት እና ለተኳሾች አቅጣጫ ለመስጠት ነው። “ዩክሬን የሩሲያን ያህል መሣሪያ የላትም። ድሮን ተጠቅሞ ዒላማን በመለየት አነጣጥሮ መተኮስ ትልቅ እገዛ አለው” ይላሉ ዶ/ር ሚሮን።

ይሁን እንጂ እንደማንኛውም ሸቀጥ ከመደብር የሚገዙት ድሮኖች፣ ለጦር ዓላማ ተብሎ ከሚፈበረኩት ድሮኖች ጋር የሚስተካከሉ አይደሉም። ዲጂአይ ማቪክ 30 ኪሎ ሜትር ብቻ የሚደርስ ርቀትን በመጓዝ አገልግሎት ይሰጣል። በአየር ላይ መብረር የሚችለውም ለ46 ደቂቃ ብቻ ነው።

ሩሲያ ከጦር ድሮኖች ራሷን ለመከላከል ራዳር ትጠቀማለች። መደበኛ ድሮኖችን ለመከላከል ደግሞ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ጥቅም ላይ ታውላለች ሲሉ ዶ/ር ሚሮን ይገልጻሉ። “የሩሲያ ኃይሎች ኤሌክትሮማግኔቲክ አካላትን ለይተው የሚመቱ መሳሪያዎች አሏቸው” ይላሉ። ይህ ደግሞ መደበኛ ድሮኖች ጂፒኤስ ተጠቅመው ቅኝት እንዳያደርጉ ያግዳል።

የሩሲያ ኃይሎች ኤሮስኮፕን የመሳሰሉ የበይነመረብ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ። በዚህ በመደበኛ ድሮኖቹ እና በተቆጣጣሪዎቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት ያቋርጣሉ። በዚህ ዘዴ ድሮኖቹ እንዲከሰከሱ ወይም ወደ መነሻ ስፈራቸው እንዲመለሱ ያስገድዳሉ። መረጃም እንዳይስተላለፉ ያስተጓጉሏቸዋል። እንደ ሩሲ ሪፖርት ከሆነ አንድ የዩክሬን ድሮን አማካይ የአገልግሎት ቆይታ አንድ ሳምንት ብቻ ነው።

እንደ አሜሪካ መንግሥት ከሆነ ሩሲያ አሁን ሻሂድ የተሰኙ የጦር ድሮኖችን ከኢራን እየገዛች ነው። መቀመጫቸውን የመን ያደረጉት የሁቲ ኃይሎች በሳዑዲ እና በተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ የሚገኙ ዒላማዎቻቸውን ለመምታት እነዚህን ድሮኖች ይጠቀማሉ።

አሜሪካ በበኩሏ 700 የሚጠጉ “ካሚካዚ” የተባሉ የጦር ድሮኖችን ለዩክሬን እያቀረበች ነው። እነዚህ በፈንጂዎች የተሞሉ ናቸው። ዒላማቸውን እስኪያገኙ ድረስ ሰማይ ላይ ያንዣብባሉ። የኤሎን መስኩ ስፔስ ኤክስ ኩባንያም ስታርሊንክ የተባሉ የኮሙኒኬሽን ሳተላይቶች ለዩክሬን እያቀረበ ነው። ይህ ደግሞ በመደበኛ ድሮኖች እና በተቆጣጣሪያቸው መካከል ግንኙነት ለመፍጠር ያግዛል።

ዲጂአይ ማቪክ 3 የተባለውን ድሮን አምራች ለዩክሬንም ሆነ ለሩሲያ እነዚህን በራሪዎች ማቅረቡን አቁሟል። ዩክሬን 200 የጦር ድሮኖችን ለመግዛት ገንዘብ ከለጋሾች እያሰባሰበች ነው። “እንደ ባይራክታር ቲቢ 2 ካሉ ትልልቅ ድሮኖች በተጨማሪ አነስተኛ እና የማይተጣጠፍ ክንፍ ያላቸውን ድሮኖች እያማተሩ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ገጣሚው ኢኮኖሚስት

አስናቀ ፀጋዬ

**መንገደኛው፤**
በቀዝቃዛው ብሩህ ኮከባማ ማታ
በጨለማው ሳር ላይ ተንጋልዬ ላፍታ
አንድ ሀሳብ መጣና እየተንሳፈፈ
በአእምሮዬ ጓዳ ተረማምዶ አለፈ
ከሚያንፀባርቁት የሰማይ ከዋክብት
መሀል ገባሁና ጠፋሁ እንደዘበት
መንገድ እንደሳተ ተጓዥ መንገደኛ
በባይተዋር ምድር ባይተዋር ብቸኛ
ድንገተኛ ፍርሃት ሽው አለ በልቤ
ድሮ ያለፉትና ገና የሚመጡት ምጡ ሀሳቤ
እናም ጭንቀታሙ የኔ ሰውነት
ይንቀጠቀጥ ጀመር በርዶ ቀዝቅዞት
አወኩ ይህ የዓለም የማንም አይደለም
ባዳ ነው ባይተዋር
ያልተገኘ ሚስጥር
ሁሌም ለጋ ፍጡር
ከአንድ ርቀት ድንገት እንደሄድኩ አሰብኩኝ
ከሌላ ርቀት ደግሞ እመለሳለሁኝ
ጉዞ እንዳደከመው እንደመንገደኛ እያለከለኩኝ
እነዚህን ቃላት ውስጤ መላለስኩኝ
መንገደኛ ነኝ በባይተዋር ሀገር
ተጓዥ ያለአቅጣጫ ያለመሪ በትር
መንገድ በሌለበት ባዶ እንግዳ ምድር

ይህን ግጥም የፃፉት የለየለት ገጣሚ አይደሉም። ግጥምም የሙሉ ጊዜ ስራቸው አይደለም። እንደው ሲነሽጣቸው ሃሳባቸውንና ስሜታቸውን በግጥም መግለፅ ይወዳሉ እንጂ የእርሳቸው ሙያ ሌላ ነው። እኚህ ሰው አካዳሚያዊ ሊህቅነትን ከፖለቲካ ትጋት ጋር ካዋሃዱ ጥቂት የኢትዮጵያ ምሁራን ውስጥ አንዱ ናቸው። የሙያዊ ብቃትና ማህራዊ ባለጉዳይ ጥምረት ደግሞ የእርሳቸው ስብዕና ዋነኛ መለያ ነው- ታላቁ የክፍለ ዘመኑ የኢኮኖሚክስ ምሁር ዶክተር እሸቱ ጮሌ።


‹‹ዶክተር እሸቱ ጮሌ መስከረም 1 ቀን 1936 ዓ.ም ነበር የተወለዱት። ይህ ቀን ደግሞ ለኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም ትርጉም ያለው ቀን ነው። አዎ! የአዲስ ተስፋና ቃልኪዳን መባቻ የሆነ የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ነበር። ዶክተር እሸቱ ጮሌም የተወለዱት በዚህ የተስፋና ቃልኪዳን ቀን ከኢትዮጵያና ኬኒያ ድንበር ብዙም በማትርቅ ‹‹ነገሌ ቦረና›› በምትባል አነስተኛ ከተማ ነበር የተወለዱት።

እርሳቸው ከተወለዱ ከሰላሳ አመት ገደማ በኋላ በዚቹ ከተማ የኢትዮጵያ ማእበል ማቀጣጠያ የሆነ እሳት ተጫረባት። የሚገርም የእጣ ግጥምጥሞሽ! ዶክተር እሸቱ ከቢጤዎቻቸው ተማሪዎች ጋራ ለረጅም ጊዜ የታገሉለት ለውጥ ስርአቱ ያስመረራቸው ወታደሮች አመፅ አስነስተው የበላዮቻቸውን በነገሌ አሰሩ። ከሃምሳ ሶስት ዓመታት በኋላ ደግሞ ሌላ ግጥምጥሞሽ። የዶክተር እሸቱ ጮሌ አስከሬን በዚሁ ድንበር አቋርጦ ለሶስት ዓመታት ከኖረባት ኬኒያ ወደ አዲስ አበባ መጣ።

የዶክተር እሸቱ ጮሌ የልጅነት ጊዜ በመከራ የተጀቦነ ነበር። እርሳቸውም ቢሆኑ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ሲናገሩ አይደመጡም። የሚታወቅ ጭምጭምታ ቢኖር ዶክተር እሸቱ ወላጅ አልባ ህፃን ሆነው በነገሌ ካምፕ ከሚኖሩ ወታደሮች ውስጥ አንዱ እንዳሳደጋቸው ብቻ ነው። ያም ሆኖ ዶክተር እሸቱ በብዙ የስጋ ዘመዶች ባይታደሉም በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በበርካታ ጓደኞቻቸው ተከበው ነበር የኖሩት።

በህፃንነታቸው ወላጅ አልባ የነበሩት ዶክተር እሸቱ በመጨረሻ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት እንክብካቤ ጉዳይ አማካሪ ሆነው ህይወታቸውን መፈፀማቸው ሌላው እጅግ አስገራሚ የህይወት አጋጣሚ ነው። ይህ የጀርባ ታሪክ ምንአልባትም ዶክተር እሸቱ ትዳር ከመያዛቸው በፊትና በኋላ እንኳን ለህፃናት የሚሰጡትን ፍቅር፣ እንክብካቤና እንዲሁም ከወለዱም በኋላ ከገዛ ልጆቻው ጋር ለነበራቸው መቀራረብና እጅግ የተለየ ራስን የመስጠት ፍቃደኝነት ምክንያት ሳይሆናቸው አልቀረም።

ዶክተር እሸቱ ፍፁም የተለየ ብሩህ አእምሮ ያለው ሆነው ማደጋቸው ግልፅ ነው። በዚህም ምክንያት ነበር የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከዛው ከነገሌ ቦረና እንዳጠናቀቁ ኀበዝ ተማሪዎች ብቻ ተመልምለው



ዶክተር እሸቱ ጮሌ፤

ይገቡበት በነበረው ምርጡ ጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጠው ቦታ ለማግኘት የበቁት። በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በዛ ዘመን የነበረውን የሀብታም ተማሪዎች ህይወት እየተካፈሉ፤ በበኩላቸው በአካዳሚክ ትምህርትም ሆነ በተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴዎች የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ቀጠሉ።

በመደበኛ ሆነ በተጓዳኝ ትምህርት ዶክተር እሸቱ በልከኛ ሚዛን እኩል እየተካፈሉ መምራት ችለው ነበር። በተማሪዎች መማክርት የተለያዩ ኃላፊነቶች ይዘዋል። በተመሳሳይ በአካዳሚክ ትምህርትም መሪ ወይም ሰቃይ ተማሪ ሆነው ቀጥለዋል። የተጓዳኝ ትምህርት ተሳትፏቸውም የስነ ፅሁፍ ዝንባሌያቸውን አውጆላቸዋል።

‹‹ሰምቲንግ›› በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይወጣ በነበረው የስነፅሁፍ መፅሄት የመጀመሪያው ተማሪ ኤዲተር ሲሆኑ በዚህም መፅሄት በርካታ ግጥሞቻቸውን አስነብበዋል። በ1958 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የተማሪነት ህይወታቸው ከፍተኛና ምርጡ ዘመን ነበር። አመቱ ሲጀመር አራት ኪሎ የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የልብ ትርታ የነበረው የአርት ፋክልቲ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ዋና ጽህፈት ቤት ወደ ስድስት ኪሎ እንደተዘዋወረ የዋናው ካምፓስ የተማሪዎች መማክርት /MCSU/ ሲቋቋም ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ።

በ1959 ትምህርት ዘመን ዶክተር እሸቱ በኢኮኖሚክስ የባችለር ዲግሪ በማዕረግ ተመርቀው የአርት ፋኩልቲ ልዩ ተማሪ በመሆን የቻንስለሩን የወርቅ ሜዳሊያ ተሸልመዋል። ከዩኒቨርሲቲው ሲመረቁም የተማሩበት የኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ግራጁዌት አሲስታንት አድርጎ አስቀራቸው።

የድህረ ምረቃ ጥናት ከኤሊኖ ዩኒቨርሲቲ በ1960 ያገኙትን የማስትሬት ዲግሪ፣ ሳይራኩስ ዩኒቨርሲቲ በ1965 ዓ.ም ያገኙትን የፒ ኤች ዲ ዲግሪና ከፍተኛ የሙያ ብቃት ክህሎት ብቻ አይደለም ለዶክተር እሸቱ ጮሌ የሰጣቸው ወይም ያስገኘላቸው። ነገር ግን በተማሪዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የነበራቸውን መስተጋብር እንዲቀጥሉበትም ነበር ያደረገው። በዚህ ረገድ ካከናወኗቸው ዋና ዋና ተግባሮች ዋናውና መጠቀስ ያለበት በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 19ኛው ጉባኤውን በሎስአንጀለስ በ1963 ዓ.ም ባደረገበት ወቅት ነው።

ይህ ምን አልባትም ዶክተር እሸቱ በተማሪዎች ፖለቲካ ውስጥ የነበራቸውን መካከለኛ ቦታ የሚያሳይ ሳይሆን አልቀረም። በኮንግረንሱ በብሄር ጥያቄ ላይ በተወሰዱት የተለያዩ አቋሞች ሳቢያ ምሬትና ቁጣ እየጨመረ ነበር።

‹‹የደርግ ዘመን በዶክተር እሸቱ ጮሌ ላይ የሚነበብ መከራና ስቃይ ቢያደርስበትም ቅሉ በተገላቢጦሽ ሲታይ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ያን ዘመን በህይወት ቆይቶ ማለፉ በአንፃሩ እደለኛ ነው ማለት ይቻላል›› ይላሉ የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ። ‹‹ሌሎች ብዙዎች አልቀዋል። ልክ እሸቱ ከአብዮት መፈንዳት ሶስት ዓመት በፊት በተነበየው መልክ።››

የ1966 ዓ.ም አብዮት የመጀመሪያዋ ዓመት ርእሰ ጉዳዮች የተጀመረው ድራማ መሀል መድረክ ላይ ዶክተር እሸቱን ደነቀሯቸው። የነበረው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር እጅግ ወግ አጥባቂ መሆናቸው ስልተሰማው አስተሳሰባቸውን ከሚጋሯቸው

> **የ1983 ዓ.ም ሁኔታን ዶክተር እሸቱ ከአካዳሚያዊ ህይወታቸው ጋር የሚጣመሩበትንና ለረጅም ጊዜ ይመኙ የነበረውን አመቺ ጊዜ የተፈጠረላቸው አድርገው ነበር የቆጠሩት። የአዲስ አበባን የኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ለማጠናከርና በተለይም የኢኮኖሚስትን ሙያ ባጠቃላይ ለማሳደግ ሙሉ ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን ሰጡ**

ወዳጆቻቸው ጋር ‹‹ዘ ፎረም›› በሚል የሚታወቀውን ቡድን አቋቋሙ። ፎረሙ ከተማሪዎችና ከሰራተኛ መሪዎች ጋር በማበር ደርግ የአፄ ኃይለሥላሴን መንግስት ከጣለ በኋላ ስልጣን የመጠቅለሉን ሁኔታ በፅኑ መቃወም ያዙ።

እነዚህ ተቃዋሚዎች ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እንዲመሰረት ጥርጊያ ጎዳና የሚያመቻች ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ጠየቁ። እንደሚጠበቀውም ደርግ ዶክተር እሸቱን በጣም አደገኛ ከሆኑ ጠላቶች አንዱ በማድረግ አነጣጠረባቸው። ስልጣኑን ባረጋገጠ በወሩ ወህኒ ጨመራቸው።

እስራቱንም መረር ለማድረግ አብዮቱን ከቀሰቀሱት የተማሪዎች ንቅናቄዎች መሪዎች እንደአንዱ በሚቆጥሩትና በጥላቻ አይን ከሚመለከቱት ንጉሳዊ ቤተሰቦችና ፅኑ ደጋፊዎች ጋር ነበር እንዲታሰር የተደረጉት። በመጨረሻም ደርግ ለህዝቡ ግፊት እጅ ሰጠና እ.ኤ.አ በ1967 ዶክተር እሸቱን ከእስር ቤት ለቀቃቸው።

የዩኒቨርሲቲ ባልደረቦቻቸው ዶክተር እሸቱ የአርት ፋክልቲ ዲን እንዲሆን በመምረጥ ለእርሳቸው ያላቸውን ክብር አሳዩ። ይህን ጊዜ ደርግ ዘዴውን በመለወጥ ግብረአበሩ ሊያደርጋቸው ፈለገ። በ1968 ዓ.ም ደርግ የማርኪሲስት ሌኒኒስት ርእዮተ ዓለምን ከብሄራዊ ዲሞክራሲዊ አብዮት ጋር ካወጀ በኋላ የህዝብ ንቅናቄና የድርጅት ጉዳዮችና አስፈላጊ ተግባሮች ለማስፈፀም ሙሉ ኃላፊነት የተሰጠውን የህዝብ ድርጅት ግዚያዊ ፅህፈት ቤት አቋቋመ።

እንደግራ ዘመም ምሁርነታቸው ይህን ተልእኮ ለማስፈፀም ዶክተር እሸቱ ተመረጡ። ምርጫውን እርሳቸው የሚቀበሉት ሆኖ አላገኙትም። በጅቡቲ በኩል በአስቸጋሪ ሁኔታ በመጓዝ ከሀገር ለመሰደድ ከባድ ውሳኔ አሳለፉ።

ጂቡቲ ብዙ ሳይቆዩ ወዲያውኑ ወደሀገራቸው መመለሳቸው ምንአልባት የህይወታቸው እጣ ክፍል ትልቁ ውሳኔ ነበር። የመመለሳቸው ሁኔታም ግልፅ አልነበረም። ወደሀገራቸው ከተመለሱ በኋላም ዩኒቨርሲቲ ዳግም ገብተው ስራቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ከሰባት ወር በኋላ ባላወቁት መንገድ እንደገና ታሰሩ። በመጨረሻ ከስር ሲፈቱ የተሰጣቸው ወረቀት በፀረ አብዮት ጥርጣሬ እንደታሰሩና አሁን ግን በምህረት መለቃቀቻቸውን ይገልፃል።

በ1975 ዓ.ም ዶክተር እሸቱ ከእስር ቤት ሲፈቱ እለቱ ከሰላሳ ሰባተኛ አመታቸው ጋር ገጥሞ ነበር። ይህም በዶክተር እሸቱ ምሁራዊ ህይወት አዲስ የተጋድሎ ምዕራፍ አበሰረ። ዶክተር እሸቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር የሙሉ ጊዜ ስራና በጥናትና ምርምር መጠመዱ ሁሉንም ነገር አስረሳው። በመጨረሻ የደርግ የመጨረሻ የህይወት ማቆያ ሙከራ የነበረውን የብሄረሰቦች ኢንስቲትዩት ሲያቋቁም ዶክተር እሸቱን ጠልፎ ከ1976 እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የኢንስቲትዩቱ የኢኮኖሚክስና የጂኦግራፊ ዲፓርትመንት ኃላፊ አደረጋቸው።

ይህ አምካኝ የሆነ የስራ ምደባ ግን ዶክተር እሸቱን ምሁራዊ ተግባራቸውን ከማከናወን በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የማማከር ስራ ከመስራት ሊገድባቸው አልቻለም። በብዙ ወርክሾፖች፣ ሴሚናሮችና ዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶች ይካፈሉ ነበር። በፓሪስና ሞስኮ የተደረጉትን ዘጠነኛውንና አስረኛውን የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጥናት ኮንፍረንሶችን ጨምሮ በሁለቱም ኮንፍረንሶች ላይ ያቀረቧቸው የኢትዮጵያን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች የሚገልፁ ጥናቶች ከኮንፍረንሶቹ ደማቅ ክስተቶች መካከል ነበሩ።

በዚሁ ጊዜ የምስራቅ አፍሪካ ሶሻል ሳይንስ ምርምር ድርጅት በምክትል ፕሬዚዳንትነት በኋላ ደግሞ የበላይ ፀሃፊ በተጨማሪ የምስራቅ አፍሪካ ሶሺያል ሳይንስ ምርምር ሪቪው አዘጋጅም በመሆን ሰርተዋል። አያሌ የምርምና ጥናት ፅሁፎችንም በብዛት ያመረቱትም በዚሁ ጊዜ ነበር።

የ1983 ዓ.ም ሁኔታን ዶክተር እሸቱ ከአካዳሚያዊ ህይወታቸው ጋር የሚጣመሩበትንና ለረጅም ጊዜ ይመኙ የነበረውን አመቺ ጊዜ የተፈጠረላቸው አድርገው ነበር የቆጠሩት። የአዲስ አበባን የኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ለማጠናከርና በተለይም የኢኮኖሚስትን ሙያ ባጠቃላይ ለማሳደግ ሙሉ ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን ሰጡ።


ከአብዮቱ በፊት በቀድሞ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ ከአርት ፋክልቲ ጠንካራ ከሚባሉ ዲፓርትመንቶች ውስጥ አንዱ ነበር። ሆኖም በአብዮቱ ዘመን እንደሌሎቹ ብዙ የሶሻል ሳይንስ ዲፓርትመንቶች ሁሉ በአይዲዮሎጂና በፖለቲካ ወረራ ተጠቅቶ ምሁራኑ እንዲመናመኑና የአካዳሚክ ተቋሙ እንዲዛባ ተደርጎ ነበር። የዚህ የዶክተር እሸቱ የአካዳሚክ አዲስ ዘመን ምዕራፍ ከፍታ ነጥብ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር እንደሚሰረት ማድረጋቸው ነበር። እርሳቸውም የማህበሩ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠው እስከ 1986 ዓ.ም አገልግለዋል።

ዶክተር እሸቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና የምርምር ኢንስቲትዩት ለሆነው ለኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት የቅርብ ደጋፊ ነበሩ። በየሶስት አመቱ በሚከናወነውና ከሁለት መቶ በላይ ተሳታፊዎች ከተለያዩ የአለም ክፍል የሚካፈሉበት የኢንስቲትዩት ኮንፍረንስ ላይ ያለማቋረጥ ሁነኛ ተሳታፊ ብቻ አልነበሩም። የኮንፍረንሶቹ አለም አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ከሆኑ ሁለት ኢትዮጵውያን አንዱ ሆነውም ሰርተዋል። እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ ጆርናል፤ ጆርናል አፍ ስተዲስ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባልም ነበሩ።

ከብሄራዊና አካባቢያዊ ሀገራት አልፈው በአህጉራዊ የምርምር መረብ ውስጥም ይሳተፉ ነበር። የአፍሪካ ማህበራዊ ጥናት ዴቨሎፕመንት ካውንስል ውስጥ በትጋት ከመሳተፍም በላይ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አባል በመሆን ለሶስት አመታት አገልግለዋል።

በ1984 ዓ.ም በፕሪስተን ዩኒቨርሲቲ የውድሮው ዊልሰን ስኩል አፍ ፐብሊክ ኤንድ ኢንተርናሽናል አፌይርስ ታጋባዥ ተባባሪ ፕሮፌሰር ሆነው ጥቂት ካሳለፉ በኋላ በዩኒሴፍ የምስራቅና ደቡብ አፍሪካ ቢሮ የኢኮኖሚ አማካሪ በመሆን ናይሮቢ ከትመው የመጨረሻ የህይወታቸውን አመታት የዓለም ህፃናትን በተለይም የአፍሪካ ህፃናትን ጉዳይ ለማሰብና እነሱን ለመንከባከብ ሰጠ። በመጨረሻም ዶክተር እሸቱ ጮሌ በርካታ የእድሜ ዘመናቸውን ለሙያቸው ሰጥተውና በተለይ በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ ለሀገራቸው ትልቅ አሻራ አሳርፈው ሰኔ 14 ቀን በ1990 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

# ስፖርት





## ጀግኖቹ በመስቀል አደባባይ ደማቅ አቀባበል ይጠብቃቸዋል

በ18ኛው የኦሪገን የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና 4 የወርቅ፣4 የብርና 2 የነሐስ ሜዳሊያ በማስመዝገብ ከአለም ሁለተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ሆኖ ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ልኡካን ቡድን አስደሳች የአገር ቤት ጉዞውን ዛሬ ይጀምራል።

ቡድኑ ዛሬ ማክሰኞ ሀምሌ 19/2014 ከፖርትላንድ ኦሪገን ተነስቶ ወደ ኒውዮርክ ይጓዛል። ኒውዮርክ ላይ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አመራሮች በተገኙበት አቀባበል ተደርጎለትም ወደ አገር ቤት የክብር ሽኝት ይጠብቀዋል።

ከኒውዮርክ ቆይታው በኋላም በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ የሚበር ሲሆን ነገ ረቡዕ ሀምሌ 20/2014 ምሽት 3 ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል።

ልዑካን ቡድኑ በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርስ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ይደረግለታል። በስካይላይት ሆቴል አርፎ ሌሊቱን ካሳለፈ በኋላም ሀሙስ ሀምሌ 21/2014 ጠዋት በክፍት አውቶቢስ ከስካይላይት ሆቴል ወደ መስቀል አደባባይ ይጓዛል።

ከረፋድ ጀምሮም በመስቀል አደባባይ የጀግና አቀባበል ይደረግለታል። ከመስቀል አደባባይ ስነስርዓት በኋላም ለቡድኑ የምሳ ፕሮግራም በአንድነት ፓርክ ተከናውኖ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበሉ እንደሚጠናቀቅ ታውቋል።

ኢትዮጵያ በቻምፒዮናው በነበራት ተሳትፎ ታምራት ቶላና ጎተይቶም ገብረስላሴ ማራቶን፣ ለተሰንበት ግደይ 10ሺ፣ ጉዳፍ ጸጋይ 5ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ሲያስመዘግቡ፣ የብር ሜዳሊያዎቹን ለሜቻ ግርማ 3ሺ ሜትር መሰናክል፣ ሞስነት ገረመው በማራቶን፣ ወርቅውሃ ጌታቸው 3ሺ ሜትር መሰናክልና ጉዳፍ ጸጋይ 1500 ሜትር አስመዝግበዋል። ሁለቱን የነሐስ ሜዳሊያዎች ደግሞ ዳዊት ስዩም 5ሺ ሜትርና መቅደስ አበበ 3ሺ ሜትር መሰናክል ማስመዝገባቸው ይታወሳል።

## ኬር ኦድ- የኢትዮጵያ የጎዳና ላይ ሩጫ አንዱ እሴት

ቦጋለ አበበ

ኢትዮጵያ የበርካታ ከዋክብት አትሌቶች ምድር ናት። በዚያ ልክ ግን አንድም የአለም ኮከብ የሆነ አትሌት የሌላቸው አገራት በብዛትም በጥራትም የሚያካሂዱት የጎዳና ላይ ውድድር በስፋት የላትም። በኢትዮጵያ ወጥ የሆነና በጥራት ደረጃም ትልቅ የሚባለው የጎዳና ላይ ውድድር ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ነው። ሌሎች የጎዳና ላይ ውድድሮች በተለያዩ አካባቢዎች ሲካሄዱ ቢስተዋልም ወጥ ሆነው ሲቀጥሉ አይታዩም። የጥራት ደረጃቸውም ጥያቄ ይነሳበታል።

በቅርብ አመት ውስጥ ተመስርቶ በጣት በሚቆጠሩ ውድድሮች ብቻ የተሻለ የጥራት ደረጃን ይዞ ብቅ ያለው "ኬር ኦድ" የጎዳና ላይ ውድድር ግን ለኢትዮጵያ የጎዳና ላይ ውድድር አንዱ እሴት የመሆን ትልቅ ተስፋ እንዳለው አሳይቷል።

ኬር ኦድ የጎዳና ላይ ሩጫ በአለም ላይ ታዋቂ በሆኑ የጉራጌና አካባቢው ኢትዮጵያውያን ተወላጅ አትሌቶች እንዲሁም ታዋቂ በሆኑ የአካባቢው ተወላጅ ሰዎች በጋራ ሆነው የመሰረቱት ውድድር ነው። ከአንድ አመት በፊት በወልቂጤ የ15 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር በማድረግ የጀመረው ኬር ኦድ የጎዳና ላይ ሩጫ ከወር በፊትም በተመሳሳይ ወልቂጤ ላይ ሁለተኛውን ውድድር በማድረግ ለበርካታ አትሌቶች የውድድር እድል መፍጠር ችሏል። ባለፈው እሁድ ደግሞ በቡታጅራ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ የ10 ኪሎ ሜትር የተሳካ ውድድር ማድረግ ችሏል። በዚህም ባለፉት ሁለት ውድድሮች የነበሩ ክፍተቶችን በማረም የጥራት ደረጃውንና የሽልማት መጠኑን በማሳደግ ወደ ፊት ትልቅ



በቡታጅራ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው ውድድር ከ20ሺ በላይ ሰው ተሳትፏል፣

ተስፋ የሚጣልበት ሆኗል።

**ኬር ኦድ የሚለው ቃል ከጉራግኛ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን**

ትርጉሙም ሰላምን ማብሰር ማለት ነው። ይህን መሪ ቃል መሰረት አድርጎ በቡታጅራ በተካሄደው ውድድርም ከተለያዩ ክለቦች፤ የአትሌት ማኔጅመንቶች፤ እና በግል የሚሮጡ ከአንድ ሺ በላይ ስመ ጥርና ታዋቂ አትሌቶች ተሳትፈውበታል። ከሃያ ሺ በላይ የአካባቢው ሕዝብም ታሪካዊቷ ኦሊምፒያን አትሌት ጌጤ ዋሚ በክብር እንግድነት በተገኘችበት ውድድር ላይ ተሳታፊ ሆኗል። በድምቀትና በስኬት ለተጠናቀቀው ውድድርም የኬር ኦድ ፕሬዚዳንት አሰልጣኝ ተሰማ አብሽሮ ለቡታጅራ ህዝብ ምስጋናውን አቅርቧል።

በውድድሩ ከ1ኛ እስከ 6ኛ የወጡ አትሌቶች ከሰላሳ እስከ ስድስት ሺ ብር የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የ10 ኪሎ ሜትር ውድድሩን በወንዶች ሀለፎም ተስፋዬ ቀዳሚ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ጀምቤሳ ደበሌ፣ ተሰማ መኮንን፣ ምትኩ አያሌው፣ አብራራው ምስጋናውና ሀብታሙ ብርሌው ተከታዮቹን ደረጃዎች ይዘው ማጠናቀቅ ችለዋል። በሴቶች መካከል የተካሄደውን ተመሳሳይ ፉክክር ደግሞ የኔነሽ ሽመክት ቀዳሚ በመሆን አጠናቃለች። እቴነሽ አላምረው፣ ዘውዲቱ አደራው፣ ጥሩዬ መስፍን፣ ሰናይት ጌታቸውና አለምገነት ሞላ ተከታትለው በመግባት የገንዘብ ሽልማቱን እንደየደረጃቸው ተቀብለዋል።

## የአክሲዮን ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በኮ/መ/ ቁጥር 81360 በሰጠው ውሣኔ መሠረት በአክሲዮኑ በአቶ ባህሩ ጋረደው ወ/አማኑኤል ስም ተመዝግበው የሚገኙትን 272 አክሲዮኖች በሀራጅ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በሀራጁ መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 25 ቀናት ውስጥ የመወዳደሪያ ሰነዶቻችሁን በማቅረብ መጫረት ትችላላችሁ፡፡

**ተጫራቾች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች፡-**

1. በጨረታው ላይ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በመሳተፍ መግዛት ይችላል፡፡
2. የአንድ አክሲዮን ጨረታ መነሻ ዋጋ ብር 1000 (አንድ ሺ) ነው፡፡
3. ተጫራቾች መጫረት የሚፈልጉትን አክሲዮኖች ለዋጋ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ከጨረታው ቀን በፊት ቄራ መላቅ ህንጻ በሚገኘው የአክሲዮኑ መስሪያ ቤት 3ኛ ፎቅ በመገኘት ከሐምሌ 21 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጨረታ ሠነዶቹን በመውሰድ መሙላትና በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 06፡00 ሰዓት ድረስ በአክሲዮኑ አስተዳደር ክፍል ማስገባት አለባቸው፡፡
4. ጨረታው ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸውና የሚመለከታቸው ታዛቢዎች በሚገኙበት በአክሲዮኑ ጽ/ቤት ይከፈታል፡፡
5. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ የተጫረቱትን አክሲዮኖች የመነሻ ጥቅል ዋጋ ¼ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. አንድ ተጫራች ሌላ ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡
7. ተጫራቾች ዜግነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ መንጃ ፍቃድ፣ ፖስፖርት ወይም ተቀባይነት ያለው ሌላ ማስረጃ ኮፒ እንዲሁም ድርጅቶች ከሆኑ የመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም ተቀባይነት ያለው ሰነድ ኮፒ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
8. የጨረታው አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ የጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ከተገለፀላቸው ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት(15) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለአክሲዮኑ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ገቢ ለማያደርጉ ተጫራቾች ጨረታው ተሰርዞ ያስያዙት ገንዘብ አይመለስላቸውም፡፡
9. በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ውጤቱ እንደታወቀ ለአክሲዮኑ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና ወዲያውኑ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፣
10. በሌሎች ሕጎችና በንግድ ህጉ የተደነገጉ ሕጎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡
11. ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0114- 70 12 82/0911-35 69 42 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።

**ሕብረት ልኳንዳ ነጋዴዎች አ.ማ.**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ካጂዩ ፒያ ሎጂስቲክ ኮ/ሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-43433 የተሽከርካሪው አይነት ሌላ የሻንሲ ቁጥር LZZ5CLSB69A429793 ሞዴል zz4257s3241V የሞተር ቁጥር 091107021927 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 11/11/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኃይሉ ደመቀ ማሞ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A25240 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MMBCNK7401D008095 ሞዴል K94TGCENXFL6 የሞተር ቁጥር 4D56-AS5494 የሊብሬ ቁጥር 211873 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 11/11/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሰላማዊት ጃንበር ተክሌ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-83046 የተሽከርካሪው አይነት ሌላ የሻንሲ ቁጥር WJMS2NSJ004185749 ሞዴል 440ETZ የሞተር ቁጥር 8210.42L* 4620-472187* የሊብሬ ቁጥር 0259097 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/10/2014ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥመሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ን/ስ/ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብርሃነ ሸዋ - የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-0314 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር TS1002-319264 ሞዴል TS100 የሞተር ቁጥር TS1002-190945 የሊብሬ ቁጥር 360967/04944 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 11/11/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**